በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የገንዘብ ሚኒስቴር
FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
MINISTER OF FINANCE

ቁጥር / Ref. No. 7/2-1/2/114
ቀን / Date 17/10/2017

ለጠቅላይ ሚኒስትር ፅ/ቤት
<u>አዲስ አበባ</u>

የፌዴራል የገቢ ግብር አዋጅን ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ይህንኑ የሚወስን የአዋጅ ረቂቅ በመ/ቤታችን ተዘጋጅቷል፡፡

ስለዚህ የአዋጁ ረቂቅ በሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት ታይቶ እንዲፀድቅ የተዘጋጀውን የአዋጅ ረቂቅ የአማርኛና እንግሊዝኛ ቅጂ ከነመግለጫው ከዚህ ጋር አባሪ አድርገን መላካችንን እንገልፃለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

አህመድ ሺዴ
ሚኒስትር

እንዲያውቁት፣
ለክቡር የፊስካል ጉዳዮች ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ (ያለ አባሪ)
<u>አዲስ አበባ</u>

# በገቢ ግብር አዋጅ ማሻሻያ ላይ የተዘጋጀ አጭር መግለጫ

1. መግቢያ

የመካከለኛ ዘመን የገቢ ስትራቴጂ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ጸድቆ ከ2017 የበጀት አመት ጀምሮ ስትራቴጂውን መሰረት በማድረግ በርካታ ተግባራት በመከናወን ላይ እንደሚገኙ ይታወቃል። የስትራቴጂው ዋንኛ አላማዎች ከ2017-2020 ባለው የስትራቴጂው ዘመን መንግስት ከግብር እና ቀረጥ የሚያገኘው ገቢ ከመታዊ ጠቅላላ ምርት ጋር ሲነጻጸር ያለውን ድርሻ በየአመቱ በአንድ የመቶኛ ነጥብ በማሳደግ በአራት አመት ጊዜ ውስጥ የግብር እና ቀረጥ ገቢ ከአመታዊ ጠቅላላ ምርት ያለውን ድርሻ ወደ 11% ማድረስ እንዲሁም የግብር እና የቀረጥ ስርአታችን ዘመናዊ እና የኢኮኖሚውን እድገት የሚያግዝ እንዲሆን ማስቻል ነው።

የፌዴራል የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 979/2008 ማሻሻያ የመንግስትን ገቢ አሰባሰብ ለማሻሻል፤ የታክስን ፍትሃዊነት ለማረጋገጥ፤ የታክስ ህጎች እንዲከበሩ ለማድረግ መንግስት በስትራቴጂው የነደፈው ሰፊ የታክስ ማሻሻያ አጀንዳ አንድ ክፍል ነው።

የፌዴራል የገቢ ግብር አዋጅ ስራ ላይ ከዋለ ከ9 አመታት በላይ ያሳለፈ በመሆኑ ካለንበት የኢኮኖሚ ሁኔታ እና ከንግዱ ውስብስብ ባህሪ አንጻር ሲታይ በርካታ ክፍተቶች ያሉበት በመሆኑ ከምንገኝበት የኢኮኖሚ ሁኔታ በተለይም ከዲጂታል ኢኮኖሚው ጋር የተጣጣመ ዘመናዊ የታክስ መሰረት እንዲኖር ማድረግ እና ለታክስ ማጭበርበር በር የሚከፍቱ አሰራሮችን መቀየር አስፈላጊ ይሆናል።

በዚህም መሰረት እነዚህን ለውጦች ተግባራዊ ማድረግ እንዲቻል በስራ ላይ ያለውን የገቢ ግብር አዋጅ የሚያሻሽል አዋጅ ከዚህ አጭር መግለጫ ጋር ተያይዞ ቀርቧል።

2. የማሻሻያው አላማዎች

የገቢ ግብር አዋጅ ማሻሻያ የሚከተሉት ሰባት አላማዎች ያሉት ነው፦

2.1 ዝቅተኛ ገቢ ያለው የህበረተሰብ ክፍል የሚያርፍበትን የግብር ጫና መቀነስ፤

2.2 የግብር መሰረትን ማስፋት፤

2.3 የግብር ስርአቱ ላይ የሚታዩ የፍትሃዊነት ችግሮችን መቅረፍ፤

2.4 የአነስተኛ የንግድ እንቅስቃሴዎች የግብር አከፋፈል ስርአት ቀላል እንዲሆን ማድረግ፤

2.5 ካፒታልን በማቀናጀት ለኢንቬስትመንት የሚውል ለማዋል የሚደረገውን ጥረት ማገዝ፤

2.6 የታክሱን መሰረት ለመሸርሸር እና ታክስ ለማጭበርበር በር የሚከፍቱ አሰራሮችን መከላከል፤

2.7 ግልጽነት በሚጎድላቸው አንቀጾች ምክንያት የሚፈጠረውን ውጣ ውረድ ማስቀረት፤

## 3. የማሻሻያው ሂደት

### 3.1 ጥናቶች

ለማሻሻያው መሰረት የሆኑ ሁለት ጥናቶች ተደርገዋል:: የመጀመሪያው የአገራችንን ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ባለሙያዎች በመጠቀም የተከናወነ ሲሆን፤ በጥናቱ ላይ አስተያየት የማሰባሰቢያ መድረክ ተዘጋጅቶ ከተለያየ የሙያ መስክ የመጡ ባለሙያዎች አስተያየት እንዲሰጡበት ተደርጓል::

በመቀጠል ይህንን ጥናት ለማዳበር በውስጥ ባለሙያዎች ዝርዝር ጥናት ተካሒዶ የመጨረሻው የጥናት ሪፖርት ተዘጋጅቷል::

### 3.2 ከባለድርሻ አካላት ጋር የተደረገ ውይይት

ጥናቱን መሰረት በማድረግ የገቢ ግብር አዋጅን ማሻሻል የሚያስችል ረቂቅ ከተዘጋጀ በኋላ በረቂቁ ላይ በተለያዩ መድረኮች ከገቢዎች ሚኒስቴር ባለሙያዎች፤ ከክልል መንግስታት የገቢዎች ቢሮ እና የፋይናንስ ቢሮ ሃላፊዎች እና ባለሙያዎች ጋር ውይይት ተድርጓል:: በእነዚህ መድረኮች የተሰጡ ጠቃሚ አስተያይቶችን በማካተት የአዋጁ ረቂቅ እንዲዳብር ከተደረገ በኋላ ተሻሽሎ በተዘጋጀው ረቂቅ ላይ ከሙያ ማህበራት፤ ከከፍተኛ የትምህርት ተቋማት እና ከንግዱ ማህበረሰብ አባላት ጋር ሰፊ ውይይት ተካሂዷል::

በመጨረሻው የህዝብ አስተያየት መስጫ መድረክ የተሰጡ አስተያየቶች ከሞላ ጎደል በተዘጋጀው ረቂቅ ውስጥ የተካተቱ ሲሆን፤ ከግብር ነጻ የሚሆነው ከመቀጠር የሚገኝ ገቢ በከፍተኛ መጠን እንዲያድግ የቀረበው ሃሳብ በዚህ ምክንያት የሚታጣውን የመንግስት ገቢ ከግምት ውስጥ ያላስገባ እና በሌላ ገቢ ሊካካስ በማይችልበት ደረጃ ገቢን የሚቀንስ በመሆኑ ለመቀበል አልተቻለም::

## 4. የአዋጁ ማሻሻያ ዋና ዋና ገጽታዎች

### 4.1 ከመቀጠር፤ ከቤት ኪራይ እና ከግለሰብ ንግድ ስራ የሚገኝ ገቢ ግብር

በስራ ላይ ባለው የገቢ ግብር አዋጅ ውስጥ የተካተቱት የግብር ማስከፊያ ሰንጠረዦች ከ1994 ዓ.ም ጀምሮ ስራ ላይ የዋሉ ሲሆን፤ የማስከፈያ መጣኔው እና የገቢ ቅንፋ (income bracket) አሁን ካለው የገንዘብ የመግዛት አቅም ጋር የሚሄዱ አይደሉም::

ይሁን እንጂ ከመንግስት ገቢ በተለይም ከክልል መንግስታት ገቢ ውስጥ ከመቀጠር ከሚገኝ ገቢ ላይ የሚሰበሰበው ትልቅ ድርሻ ያለው በመሆኑ መጣኔውን መቀነስ ወይም የገቢ ቅንፉን ማሳደግ በመንግስት በተለይም በክልል መንግስታት ገቢ ላይ ከፍተኛ ጫናን የሚያሳድር በመሆኑ በጥንቃቄ መታየት አለበት።

በመሆኑም ተቀጣሪው በኑሮ ውድነት ምክንያት ያለበትን ጫና በአንድ በኩል፤ የመንግስት ገቢ በከፍተኛ ደረጃ መሸርሸር በመንግስት አገልግሎቶች ላይ የሚያሳድረውን ተጽእኖ በሌላ በኩል ከግምት ውስጥ በማስገባት ሰንጠረዦቹ ላይ ሚዛኑን የጠበቀ ማስተካከያ ተደርጓል።

በዚህም መሰረት በማሻሻያው ከግብር ነጻ የሚሆነውን ከመቀጠር የሚገኘውን ገቢ በ300% በማሳደግ ወደብር 2,000 (ሁለት ሺህ ብር)፤ ከፍተኛው የማስከፈያ መጣኔ የሆነው 35% የሚያርፍበት ከመቀጠር የሚገኝ ገቢ ደግሞ ወደብር 14,000 (አስራ አራት ሺህ ብር) ከፍ እንዲል ሆኗል።

በተመሳሳይ የታክሱን ፍትሃዊነት ለማስጠበቅ ከግብር ነጻ የሚሆነው ከኪራይ እና ከግለሰብ ንግድ (sole proprietor) የሚገኘው አመታዊ ገቢ በዚሁ ልክ ተስተካክሏል።

በግብር ማስከፈያ ሰንጠረዦች ላይ በተደረገው ለውጥ ምክንያት መንግስት የሚያጣው ገቢ የአገራዊ ጠቅላላ ምርት 0.21% ሲሆን ከዚህ በላይ ማስተካከያ ይደረግ ቢባል በመንግስት አገልግሎቶች ላይ ከፍተኛ አሉታዊ ውጤትን የሚያስከትል ይሆናል።

በሚደረገው ማሻሻያ ምክንያት የሚታጣውን ገቢ የግብር መሰረትን ለማስፋት በአዋጁ በተወሰዱ ማስተካከያዎች እና የታክስ አስተዳደሩን ውጤታማ በማድረግ ማካካስ እንዲሚቻል ታምኖበታል።

ኩባንያን ጨምሮ "ድርጅት" ተብለው በታክስ አስተዳደር አዋጁ ትርጉም ከተሰጣቸው አካላት የሚሰበሰበው ግብር በነበረበት ሁኔታ 30% (ሰላሳ በመቶ) ሆኖ የሚቀጥል ይሆናል።

## 4.2 ከዲጂታል ይዘት ፈጠራ የሚገኝ ገቢ ግብር እንዲከፈልበት ማድረግ

የማሻሻያው አዋጅ ከዲጂታል ይዘት ፈጠራ የሚገኝ ገቢ ግብር እንዲከፈልበት የሚያደርግ ነው።

በአዋጁ አንቀጽ 2(29) እንደተተረጎመው የዲጂታል ይዘት ፈጠራ ገቢ የሚባለው፦ ከዩትዩብ፤ ከማህበራዊ ሚዲያ፤ በኢንተርኔት ከሚሰራጭ መረጃ (ፖድካስቲንግ)፤ በኢንተርኔት ከሚፈጸም ግብይት (online sales) እና ከስፖንሰርሺፕ እና ከመሳሰሉት የሚገኝ ገቢ ነው።

የገንዘብ የሪከርድ አስተዳደር አገልግሎት 2 ሚኒስቴር

የዚህ አይነቱ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ በመደበኛነት የሚከናወን ከሆነ የሚገኘው ገቢ በንግድ ስራ ገቢ ስር የሚወድቅ ስለሆነ የንግድ ስራ ገቢ ግብር የሚከፈልበት መሆኑ፤ በአዋጁ የተዘረዘሩትን የማያሟላ ከሆነ ግን "ሌሎች ገቢዎች" በሚለው ስር ሆኖ ከጠቅላላ ገቢው ላይ 15% (አስራ አምስት በመቶ) ግብር እንደሚከፈልበት በአዋጁ ረቂቅ ተመልክቷል::

ለዲጂታል ይዘት አመንጪዎች ክፍያ የሚያመቻቹ መድረኮች (platforms) ለእያንዳንዱ የዲጂታል ይዘት አመንጪ የተከፈለውን ገንዘብ የሚያሳይ ሪፖርት ለታክሱ ባለስልጣን የመላክ ግዴታ ያለባቸው መሆኑን የአዋጁ ረቂቅ ይደነግጋል::

በዚህም መሰረት የዲጂታል ይዘት አመንጪዎች የታክስ ከፋይ መለያ ቀጥር የማውጣት፤ ገቢን የማስታወቅ እና ሊሎችም የታክስ ከፋይ ግዴታዎች ይኖሩባቸዋል::

## 4.3 ከዲጂታል አገልግሎት የሚገኝ ገቢ

ዘመናችን የቴክኖሎጂ ዘመን በመሆኑ ኩባንያዎች ድንበር ሳይገድባቸው የቴክኖሎጂ ውጤቶችን ይገበያያሉ:: ግብይቱ እቃ በሚሆንበት ጊዜ በጉምሩክ ጣቢያዎች በኩል ስለሚያልፍ መቆጣጠር የሚቻልበት እድል ያለ ሲሆን ከሌሎች የቴክኖሎጂ ውጤቶች በሚገኝ ገቢ ላይ ግብር መሰብሰብ ግን አስቸጋሪ ሆኖ ቆይቷል::

በተለይም የውጭ አገር የሳተላይት ቴሌቪዥን ኩባንያዎች የሶስተኛውን አለም ገበያ ተቆጣጥረው የሚገኙ ሲሆን፤ ከዚህ አይነቱ ገቢ ላይ መንግስታት ግብር የሚሰበስቡበት ምቹ ሁኔታ አልነበረም::

ይህንን ችግር ለመቅረፍ ከቅርብ አመታት ወዲህ መንግስታት ከዲጂታል አገልግሎት ታክስ የሚሰበስቡበት ራሱን የቻለ ህግ እያወጡ ታክሱን በመሰብሰብ ላይ ይገኛሉ:: በተመሳሳይም አገራችን ከዚህ አይነቱ ገቢ ግብር መሰብሰብ የሚያስችላት ድንጋጌ በአዋጁ ረቂቅ ውስጥ ተካቷል::

በዚህም መሰረት የሚኒስትሮች ምክር ቤት ከዲጂታል አገልግሎት ከሚገኝ ጠቅላላ ገቢ ላይ ከ5% ያልበለጠ ታክስ መሰብሰብ የሚያስችል ደንብ ሊያወጣ እንደሚችል፤ አሰባሰቡ እና ሌሎችም ዝርዝር ሁኔታዎች በደንቡ እንደሚወሰኑ በአዋጁ ረቂቅ ተካቷል::

## 4.4 ለአነስተኛ የንግድ ስራዎች ቀላል የግብር ስርአት መዘርጋት

አመታዊ የሽያጭ ገቢያቸው ከብር ሁለት ሚሊዮን (ብር 2,000,000) በታች የሆነ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ግብር የሚከፍሉት በአመታዊ ጠቅላላ የሽያጭ ገቢያቸው ላይ እንዲሆን የሚያስችል ቀለል ያለ ስርአት በአዋጁ ረቂቅ ተዘርግቷል::

የገንዘብ ሚኒስቴር
የሪከርድ አስተዳደር አገልግሎት
2

በዚህ ስርአት መሰረት አነስተኛ የንግድ ስራዎች ከዚህ በፊት ከነበረው እጅግ የተወሳሰበ የቁርጥ ግብር ስርአት ተላቀው አመታዊ የሽያጭ ገቢያቸው ላይ ተመስርቶ በአነስተኛ መጣኔ ከ2% እስከ 9% ግብር እንዲከፍሉ ይደረጋል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ አነስተኛ የንግድ ስራዎች ሲከፍሉት የነበረው የተርን ኦቨር ታክስ በአመታዊ ሽያጫቸው ላይ በሚከፍሉት ታክስ ውስጥ እንዲጠቃለል የተደረገ ስለሆነ የተርን ኦቨር ታክስ በሚል በተለይ ሲከፍሉ የነበረው ታክስ እንዲቀር ተደርጓል፡፡

ይሁን እንጂ በሙያ ስራ ላይ የተሰማሩ ግብር ከፋዮች አእምሮአቸውን ተጠቅመው በአነስተኛ ወጪ ስራቸውን የሚያከናውኑ በመሆኑ እቃ ገዝተው ለሚሸጡ የተዘጋጀው በጠቅላላ ሽያጭ ላይ የተመሰረተው የማስከፈያ መጣኔ ለሙያ ስራ ተፈጻሚ እንዲሆን ማድረግ ፍትሃዊ አይሆንም፡፡ በዚህም መሰረት የሙያ ስራ የሚሰሩ የሂሳብ መዘገብ አቅርበው ግብር መክፈል እንደሚገባቸው በአዋጁ ረቂቅ ተመልክቷል፡፡

## 4.5 ገቢን ስለማጣመር

ስራ ላይ ባለው አዋጅ የግለሰቦች ገቢ ተጣምሮ ግብር የሚከፈልበት ገቢው ከአንድ የገቢ አይነት የተገኘ ወይም በአንድ ሰንጠረዥ ስር የሚወድቅ ገቢ በሚሆንበት ጊዜ ብቻ ነበር፡፡ ይህ አሰራር ከተለያየ ምንጭ ገቢ የሚያገኙ ግለሰቦች ከእያንዳንዱ ምንጭ ያገኙት በመጀመርያ ቅንፍ ውስጥ የሚወድቅ ገቢ ከግብር ነጻ ስለሚሆን በጠቅላላው ግብር የማይከፍሉበት መጠን ከፍተኛ ይሆናል፡፡ ይህም የታክሱን ፍትሃዊነት ያዛባል፡፡

በመሆኑም በተለያየ ሰንጠረዥ ስር የሚወድቅ ቢሆንም ግለሰቦች ከተለያየ ምንጭ የሚያገኙት ገቢ ተጣምሮ ግብር እንዲሰላበት የሚደረግ ሲሆን፤ በዚህም ስሌት ከግብር ነጻ የሚደረገው አንድ ጊዜ ብቻ ይሆናል፡፡ ግብር ከፋዩ የፌዴራል እና የክልል ግብር ከፋይ በሚሆንበት ጊዜ በህገ መንግስቱ በተደነገገው መሰረት በክልል ካከናወነው ስራ ባገኘው ገቢ ላይ ለክልል መንግስት የከፈለው ግብር ተቀናሽ የሚደረግ መሆኑን የሚደነግጉ አንቀጾች ተካተዋል፡፡

## 4.6 አማራጭ አነስተኛ ግብር ስራ ላይ ማዋል

በፌዴራል መንግስት ደረጃ ከተመዘገቡት ታክስ ከፋዮች መካከል ከ67% በላይ የሚሆኑት ኪሳራ ወይም ምንም አልሰራንም የሚል ማስታወቂያ የሚያቀርቡ ናቸው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ምንም አልሰራንም በሚል የሚያስታውቁት ብዛት እየጨመረ ኪሳራ የሚያስታውቁት ቁጥር ደግሞ እየጨመረ መሄዱን መረጃዎች ያሳያሉ፡፡

ማናቸውም በንግድ ስራ ላይ የተሰማራ ሰው ለአመታት በኪሳራ ሊቀጥል እንደማይችል ግልጽ ነው፡፡ በሌላ በኩል ምንም ያልሰራ ከሆነ ወደኪሳራ የሚቀየር

የገቢዎች
የሪከርድ
አስተዳደር
አገልግሎት
2
ሚኒስቴር

እንጂ ባለበት የሚቀጥል ሊሆን አይችልም። በመሆኑም የተደረገው ጥናት ግብር ሳይከፍሉ የሚሰሩ በርካታ ሰዎች መኖራቸውን የሚያሳይ ነው።

በዚህ አይነት የሚያጋጥመውን ችግር ለመፍታት አገሮች የሚጠቀሙበት አሰራር ማናቸውም በንግድ ስራ ላይ የተሰማራ ግብር ከፋይ ከስሮ የንግድ ስራውን ካልዘጋ በስተቀር ለአመታት በኪሳራ ሊቀጥል ስለማይችል ከጠቅላላ ገቢው የተወሰነ መቶኛ አማራጭ አነስተኛ ግብር እንዲከፍል ማድረግ ነው።

ይህ አሰራር ከግብር ለመሸሽ ኪሳራ የሚያስታውቁ ትክክለኛውን ግብር እንዲከፍሉ በትክክል ኪሳራ ያጋጠማቸው ደግሞ መክሰራቸው ሲረጋገጥ የከፈሉት ግብር እንዲካካስ ማድረግ የሚያስችል በመሆኑ ጠቀሜታው የጎላ ነው።

በዚህም መሰረት፡-

- አስታውቀው የከፈሉት ግብር ከአመታዊ ከጠቅላላ ገቢያቸው 2.5% በታች የሆነ ግብር ከፋዮች በአመታዊ ጠቅላላ ገቢያቸው ላይ የሚታሰብ 2.5% አማራጭ አነስተኛ ግብር እንዲከፍሉ፤
- ኪሳራው ትክክል መሆኑ ከተረጋገጠ ይህ የከፈሉት ግብር በሚቀጥለው የግብር አመት ሊከፍሉት ከሚገባው ግብር ላይ ተቀናሽ እንዲደረግ፤
- ተቀናሹ የሚፈቀደው በሚቀጥለው የግብር አመት የከፈሉት ግብር ከ2.5% በላይ በሚሆንበት ጊዜ እና ከዚያ በላይ ሊከፈል ከሚገባው ግብር ላይ እንዲሆን፤
- አማራጭ አነስተኛ ግብር በአነስተኛ የንግድ ስራ ላይ የተሰማሩትን (ደረጃ "ለ") እንደማይመለከት፤
- ጠቅላላ ገቢ ሲባል ለባንኮች፤ ለመድን ኩባንያዎች፤ በኮሚሽን ለሚሰሩ፤ የእቃቸው ዋጋ በመንግስት ለሚወሰን የስራቸውን ባህሪ ከግምት ውስጥ ያስገባ እንደሚሆን፤

በአዋጁ በዝርዝር ተመልክቷል።

## 4.7 በጥሬ ገንዘብ በሚደረግ ግብይት ላይ ገደብ ስለማስቀመጥ

በአገራችን የግብር ስርአት ውስጥ ለሚታየው ከፍተኛ የታክስ መሰወር ድርጊት በር ከፋች ከሆኑት ውስጥ አንዱ በጥሬገንዘብ የሚፈጸም ግብይት ነው። ለትክክለኛ ግብር አወሳሰን መሰረቱ መረጃ ሲሆን፤ በጥሬገንዘብ የሚፈጸም ግብይት የታክሱ ባለስልጣን ስለግብር ከፋዩ ግብይት በቂ መረጃ እንዳያገኝ በማድረግ ታክስ ላለመክፈል ለሚደረገው ጥረት መሳሪያ ሆኖ በማገልገል ላይ ይገኛል።

የገንዘብ
የሪከርድ አስተዳደር አገልግሎት
2
ሚኒስቴር

እንደ ህንድ ያሉ አገሮች ይህንን ችግር ለመፍታት ከተጠቀሙበት ዘዴ አንዱ ግብር ከፋዮች ከተወሰነ ገንዘብ መጠን በላይ ለሆነ ግብይት ጥሬገንዘብ እንዳይቀበሉ በማድረግ የታክሱ ባለስልጣን የባንክ መረጃን በመጠቀም ትክክለኛ ግብር ለመወሰን የሚችልበትን ምቹ ሁኔታን መፍጠር ነው::

የእነዚህን አገሮች ምርጥ ተሞክሮ በመውሰድ፡

- በማናቸውም የእቃ እና አገልግሎት ግብይት ገገርም ሆነ ሻጭ ከብር 30,000 በላይ የሆነ ገንዘብ መቀበል እና መክፈል የማይችሉ መሆኑን፤
- ይህንን የገንዘብ መጠን በማለፍ ክፍያን ከፋፍለው የሚፈጽሙትን ለመከላከል አንድ ግብይት የሚባለው፤ በአንድ ቀን ውስጥ አንድ ሰው ከሌላ ተመሳሳይ ሰው ጋር የሚፈጽመው ግብይት፤ ለአንድ እቃ ግብይት በተለያየ ጊዜም ቢሆን የሚፈጸም ክፍያ ወዘተ መሆኑን፤
- ይህንን ተላለፎ ከብር 30,000 በላይ የተቀበለ ሰው የተቀበለውን ገንዘብ እጥፍ እንደሚቀጣ፤ የከፈለው ሰው ደግሞ የዚህ አይነቱ ወጪ ለግብር አከፋፈል በማስረጃነት እንደማይያዝለት፤
- የገንዘብ ሚኒስቴር የገንዘብን የመግዛት አቅም እና ሌሎችንም ሁኔታዎች ከግምት ውስጥ በማስገባት የገንዘቡን መጠን ከፍ ወይም ዝቅ ማድረግ እንደሚችል፤

በአዋጁ ረቂቅ ተመልክቷል::

ይህ የገንዘብ መጠን የተወሰነው ለፌዴራል መንግስት ግብር ከፋዮች ሲሆን፤ ክልሎች በሚያወጡት የገቢ ግብር አዋጅ የመስረተ ልማት አቅርቦትን ከግምት ውስጥ በማስገባት መጠኑን ከፍ ሊደርጉ ይችላሉ::

## 3.8 . ግብርን አስቀድሞ መክፈል

የማናቸውም ግብር ከፋይ ትርፍ በግብር አመቱ ውስጥ የሚያከናውነው የንግድ ስራ ድምር ውጤት እንጂ በአመቱ መጨረሻ የሚገኝ ያለመሆኑ ግልጽ ነው:: አብዛኞቹ ግብር ከፋዮች በአመቱ ውስጥ ያገኙትን ትርፍ ለተለያየ አላማ በማዋል ግብር የመክፈያ ጊዜው ሲደርስ በጥሬ ገንዘብ እጥረት ምክንያት ከፍተኛ ችግር ላይ ሲወድቁ ይስተዋላል::

በሌላ በኩል መንግስት የተፈቀደውን የወጪ በጀት ለመሸፈን የሚያስፈልገውን ገቢ በወቅቱ ስለማያገኝ የመንግስት ስራዎች አፈፃጸም እንዲዘገይ እና ህብረተሰቡ ተገቢውን የመንግስት አገልግሎት እንዳያገኝ ምክንያት ይሆናል::

እነዚህን ችግሮች ለማቃለል የሚቻለው የታክስ አከፋፈል ስርአቱ እነዚህን ችግሮች የሚያስወግድ መሆን ሲችል ነው:: በዚህም መሰረት፦

- የደረጃ "ሀ" ግብር ከፋዮች ባለፈው የግብር አመት የከፈሉትን ግብር መሰረት በማድረግ በየሶስት ወሩ ባለፈው አመት የከፈሉትን ግብር አንድ አራተኛ እንዲከፍሉ፤

- በአመቱ መጨረሻ ሊከፍሉት የሚገባው ግብር ከከፈሉት ያነሰ ከሆነ ልዩነቱን እንዲከፍሉ፤ የበለጠ ከሆነ ተመላሽ እንዲደረግላቸው፤

የሚያስችል ድንጋጌ በአዋጁ ረቂቅ ውስጥ ተካቷል::

### 3.9 ኃላፊነታቸው የተወሰነ የሽርክና ማህበራት ግብር አከፋፈል

ኃላፊነታቸው የተወሰነ የሽርክና ማህበራት (Limited Liability Partnerships) አደረጃጀታቸውን እና ገቢ የሚከፋፈሉበትን መንገድ ከግምት ውስጥ ያስገባ የግብር ስርአት ያልተዘረጋላቸው በመሆኑ ለተደራራቢ ግብር ተጋልጠዋል::

የህግ እና የሌሎችም ሙያዎች ባለቤቶች በዚህ መልክ ተደራጅተው መስራታቸው በአለም አቀፍ ደረጃ የተለመደ እና ውጤታማነትን የሚያስገኝ ስለሚሆን አደረጃጀቱ ለተጨማሪ የግብር ጫና የሚዳርግ ሊሆን አይገባም:: ይህንን ከግምት ውስጥ በማስገባት እና የሌሎች አገራትን ልምድ በማየት ማህበራቱ ከግብር ነጻ ሆነው ማህበሩ ትርፉን ለአባላቱ በሚያከፋፍልበት ጊዜ በሰንጠረዥ "ሐ" መሰረት ግብሩን ቀንሶ ለታክሱ ባለስልጣን ገቢ የሚደረግበትን አሰራር የሚዘረጋ አንቀጽ ተካቷል::

### 3.10 ኢንቬስትመንትን ለማበረታታት የሚያስችሉ ማሻሻያዎች

አንዳንድ ድርጅቶች የግለሰቦችን ሃብት በማሰባሰብ የጋራ ኢንቬስትመንት ፈንድ (ኩባንያ) (Collective Investment Scheme) በማቋቋም ይህንን ገንዘብ የካፒታል እጥረት ባለባቸው ድርጅቶች ውስጥ በኢንቬስትመንት ስራ ላይ ያውላሉ:: እነዚህ ኩባንያዎች በራሳቸው የንግድ ስራ እንቅስቃሴ ውስጥ የሚገቡ ባለመሆኑ በአብዛኛዎቹ የአለም አገሮች በታክስ አከፋፈል ረገድ የተለየ ስርአት (pass through treatment) ይዘረጋላቸዋል::

በአገራችንም የዚህ አይነት ድርጅቶች ኢንቬስትመንትን በማገዝ ረገድ ጠቀሜታ ስላላቸው ተመሳሳይ የሆነ ስርአት ሊዘረጋላቸው እንደሚገባ ታምኖበታል::

በመሆኑም በህጋዊ መንገድ ተመዝግበው የሚሰሩ የጋራ የኢንቬስትመንት ኩባንያዎች ግብር የሚከፍሉት ያገኙትን ትርፍ ለባለገንዘቦቹ በሚያከፋፍሉበት ጊዜ መሆኑን የሚገልጽ አንቀጽ ታክሏል።

ገንዘብ የሪከርድ አስተዳደር አገልግሎት 2 ሚኒስቴር

### 3.11 ከኢትዮጵያ ውጭ የሚደረግ የሃብት ዝውውር

አንዳንድ የውጭ አገር ኩባንያዎች በኢትዮጵያ ውስጥ አክሲዮን በማስተላለፍ በሚገኝ ጥቅም ላይ የሚከፈለውን ግብር ላለመክፈል ኢትዮጵያ ውስጥ የንግድ ስራ የሚሰራው ኩባንያ ባለቤት የሆነው ኩባንያ የታክስ ጫና በሌለባቸው አገራት (tax haven) በማቋቋም ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ኩባንያ አክሲዮን ሳይነካ በውጭ አገር ያቋቋሙትን እና የኢትዮጵያው ኩባንያ ባለቤት የሆነውን ኩባንያ አክሲዮን ብቻ በመሸሻጥ ከኢትዮጵያ ታክስ ይሸሻሉ።

ይህ ችግር በዋንኛነት የሚታየው በማእድን እና ነዳጅ ዘርፍ ላይ በመሆኑ የማእድን እና ነዳጅን ግብር አከፋፈል በሚዘረዝረው የአዋጁ ክፍል አፈጻጸሙን መከላከል የሚያስችል ድንጋጌ የሰፈረ ቢሆንም፤ አፈጻጸሙ በሌሎችም መስኮች በመስፋፋት ላይ ይገኛል።

በመሆኑም በዚህ አይነት አደረጃጀት ታክስ ላለመክፈል የሚደረገውን ጥረት ለመከላከል አክሲዮኑ የተላለፈው በውጭ አገር የሚገኝ ድርጅት ካለው ሃብት ውስጥ ከ50% በላይ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኝ ከሆነ የዚህ ድርጅት አክሲዮን መተላለፍ በተዘዋዋሪ መንገድ ኢትዮጵያ ውስጥ ያለውን ድርጅት አክሲዮን እንደማስተላለፍ ተቆጥሮ ግብር እንዲከፈልበት ማድረግ የሚያስችል ድንጋጌ በአዋጁ ረቂቅ ውስጥ ተካቷል።

### 3.12 ቃል ለተገባ አክሲዮን የዋለ የአክሲዮን ትርፍ ድርሻ

ኩባንያዎች የሚያገኙትን ትርፍ ለባለአክሲዮኖች በማከፋፍል ፈንታ እዚያው ኩባንያው ውስጥ ስራ ላይ እንዲውል በማድረግ ልማትን በማፋጠን ረገድ የበኩላቸውን አስተዋጽኦ ማድረግ እንዲችሉ ለማበረታታት ባለአክሲዮኖች የአክሲዮን ትርፍ ድርሻውን ከተከፋፈሉ 10% የአክሲዮን ትርፍ ድርሻ ግብር እንዲከፍሉ፤ መልሰው ኢንቬስት ካደረጉ ግን ከዚህ ግብር ነጻ እንዲሆኑ ማድረግ የሚያስችል ድንጋጌ ስራ ላይ ባለው አዋጅ ውስጥ ተካቷል።

አከራካሪ ሆኖ የቆየው ባለአክሲዮኖች ያገኙትን የትርፍ ድርሻ፤ ቃል የገቡትን አክሲዮን ዋጋ ለመክፈል ቢያውሉ ታክሱን መክፈል አለባቸው ወይስ የለባቸውም የሚለው ነው? የህጉ ዋንኛ አላማ ባለአክሲዮኖች የሚያገኙትን የትርፍ ድርሻ ወስደው ለፍጆታ ከሚያውሉ ኩባንያው ውስጥ ስራ ላይ እንዲውል በማድረግ የኩባንያውን አቅም እንዲያሳድጉ ማድረግ በመሆኑ የዚህ አይነቱ ኢንቬስትመንትም ሊበረታታ እንደሚገባ ታምኖበታል።

በዚህም መሰረት ባለአክሲዮኖች ያገኙትን የትርፍ ድርሻ ቃል የገቡትን የኩባንያውን አክሲዮን ዋጋ ለመክፈል ካዋሉ የአክሲዮን ትርፍ ድርሻ ግብር እንደማይጠየቁ የሚገልጽ ድንጋጌ በአዋጁ ውስጥ ተካቷል።

የገንዘብ የሪከርድ አስተዳደር አገልግሎት 2 ሚኒስቴር

## 3.13. በተለያዩ ህጎች የተሰጡ የግብር ማበረታቻዎች በአንድ ህግ እንዲመሩ ማድረግ

መንግስት ኢንቬስትመንትን፣ ፈጠራን፣ በማህበር ተደራጅቶ መስራትን ወዘተ ለማበረታታት የግብር ማበረታቻዎች ይሰጣል። በእነዚህ ማበረታቻዎች ምክንያት የማይሰበሰበው የመንግስት ገንዘብ ተሰብስቦ የመንግስትን የፍላጎት ቅደም ተከተል በጠበቀ አካኋን ስራ ላይ ሊውል የሚችል በመሆኑ እንደታክስ ወጪ (tax expenditure) የሚቆጠር ነው። የዚህ አይነት ወጪ በጥንቃቄ ካልተመራ የመንግስትን የገቢ አቅም የሚያዳክም ስለሚሆን ሊታጣ የሚችለውን ገቢ ከግምት ውስጥ ያስገባና በጥናት ላይ የተመሰረተ ሊሆን ይገባል። ከዚህም በተጨማሪ መንግስት በሰጠው ማበረታቻ ምክንያት የተገኘው ኤኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ጥቅም እንዲሁም የታጣው ገቢ መጠን እየተለካ የሚፈጸም ካልሆነ ለከፍተኛ ብክነት የሚዳርግ ይሆናል።

በመሆኑም ከግብር ነጻ በማድረግ የሚሰጥ ማበረታቻ ወጥነት ባለው በአንድ የታክስ ማበረታቻ ሕግ እንዲመራ ማድረግ የሚያስችል ድንጋጌ በአዋጁ ረቂቅ ተካቷል።

## 3.14 በሰንጠረዥ "መ" ገቢዎች ማስከፈያ መጣኔ ላይ ማስተካከያ ማድረግ

የሰንጠረዥ "መ" ገቢዎች የሚባሉት ከዲቪዴንድ፣ ከካፒታል ዋጋ እድገት ጥቅም፣ ከወለድ፣ ከሮያልቲ፣ ከመዝናኛ አገልግሎት እና ከእድል ሙከራ ጨዋታ የሚገኙ ገቢዎች ናቸው።

በስራ ላይ ያለው አዋጅ በእነዚህ ገቢዎች ላይ ከ5-30% በሚደርስ መጣኔ ግብር ሊከፈልባቸው እንደሚገባ ይደነግጋል። ይሁን እንጂ እነዚህ መጣኔዎች በተለያዩ የአለም አገራት በተለይም በአካባቢያችን ካሉ አገራት ጋር ሲነጻጸሩ አንዳንዱ አነስተኛ ቀሪው ደግሞ ከፍተኛ ሆኖ ይታያል። የውጭ ኢንቬስትመንትን በመሳብ ረገድ ተወዳዳሪ መሆን እንድንችል የማስከፈያ መጣኔዎቹን ማስተካከል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ የማስከፈያ መጣኔው ከ10-25% እንዲሆን በሚያስችል አይነት ተስተካክሏል።

## 3.15 ከግብር ነጻ ስለማድረግ

ዜጎች በባንክ ውስጥ ያስቀመጡት ገንዘብ በተለያየ ምክንያት ባክኖ ገንዘባቸውን ማግኘት የማይችሉበት ሁኔታ ቢፈጠር በዚህ አይነት ለሚያጋጥመው ችግር የመድን ዋስትና የሚሰጥ የተቀማጭ ገንዘብ መድን ፈንድ በሚኒስትሮች ምክር ቤት መቋቋሙ ይታወቃል። ይህ ፈንድ ለትርፍ የሚሰራ ባለመሆኑ የሚያገኘው ገቢ ከግብር ነጻ እንዲሆን የሚያስችል አንቀጽ ታክሏል።

ኩባንያዎች የፋይናንስ አቅማቸውን ለማጠናከር አዳዲስ አክሲዮን ለገበያ በማዋል ካፒታል የሚያሰባስቡ መሆኑ ይታወቃል። በዚህ አይነት ከአክሲዮን ሽያጭ የሚገኘው ፕሪሚየም ለባለአክሲዮኖች ሲከፋፈል ግብር የሚከፈልበት ሲሆን፣ የኩባንያውን የፋይናንስ አቅም ለማሳደግ የሚውል በሚሆንበት ጊዜ ግን ከግብር ነጻ እንዲሆን የሚያስችል አንቀጽ በአዋጁ ረቂቅ ውስጥ ተካቷል።

5. በአዋጁ መሻሻል ምክንያት ሊገኝ ይችላል ተብሎ የሚጠበቀው ውጤት

የገቢ ግብር አዋጅ ማሻሻያ የሚከተሉትን ውጤቶች እንደሚያስገኝ ይታመናል፦

- ከግብር ነጻ የሆነው ከመቀጠር የሚገኝ ገቢ ከፍ እንዲል የተደረገ በመሆኑ ዝቅተኛ ገቢ ባላቸው ተቀጣሪዎች ላይ የግብር ጫናው ይቀንሳል፤

- የግብር መሰረቱ እንዲሰፋ፤ ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ተቀንሶ የሚቀረው ግብር (ሠንጠረዥ "መ") መጠነኛ ጭማሪ እንዲኖረው የተደረገ በመሆኑ መንግስት ከገቢ ግብር የሚያገኘው ገቢ በአንጻራዊ ሁኔታ ከፍ እንዲል ያግዛል፤

- ለኢኮኖሚው እድገት አስተዋጽኦ ሊያደርጉ በሚችሉ መስኮች እና በአንዳንድ የአደረጃጀት አይነቶች ላይ የነበረው የግብር ጫና እንዲቀንስ የተደረገ በመሆኑ የኢኮኖሚ መነቃቃትን ይፈጥራል፤

- ግልጽነት ባልነበራቸው አንቀጾች ምክንያት በግብር ከፋዩ እና በታክሱ ባለስልጣኑ መካከል የነበረውን ያለመግባባት ይቀንሳል፤

- በአነስተኛ የንግድ ስራዎች ላይ ያለውን አስተዳደራዊ ጫና በመቀነስ የመልካም አስተዳደር ችግሮችን ይቀንሳል፤

- የታክሱን ፍትሃዊነት ማረጋገጥ የሚያስችሉ አሰራሮችን የሚዘረጋ (ገቢን ማጣመር) በመሆኑ በፍትሃዊነት ረገድ ሲታይ የነበረውን ክፍተት ይዘጋል።

6. ማጠቃለያ

በገቢ ግብር አዋጅ ላይ የተደረገው ማሻሻያ የኢትዮጵያን የግብር ስርአት ዘመናዊ በማድረግ ረገድ አንድ እርምጃ ወደፊት የሚያሻግር ሲሆን፤ የአገራችንን ኤኮኖሚያዊ ሁኔታዎች ከግምት ውስጥ ባስገባ ሁኔታ የግብር ስርአታችንን ከአለማችን ልምድ ጋር ማጣጣም የሚያስችል ነው። በተለይም በዲጂታል ዘመን በታክስ አሰባሰብ ረገድ ሊኖር የሚችለውን ፈተና ከግምት ውስጥ በማስገባት የታክስ መሰረትን ማስፋትን እና ፍትሃዊነትን ማረጋገጥን የመሳሰሉ መንታ ግቦችን ሚዛናዊ በሆነ መንገድ ተግባራዊ ማድረግ የሚያስችል ነው።

ስለዚህ ከዚህ አጭር መግለጫ ጋር ተያይዞ የቀረበው የገቢ ግብር አዋጅ ማሻሻያ ረቂቅ ስራ ላይ እንዲውል እንዲፈቀድ ቀርቧል።

## አዋጅ ቁጥር ___/2017

## የፌዴራል የገቢ ግብር አዋጅን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ

በገቢ ግብር ሥርዓት ላይ ለውጥ በማድረግ የመንግስትን ገቢ አሰባሰብ ማሻሻል እና ለኢኮኖሚው እድገት እገዛ ማድረግ የሚቻል መሆኑ ስለታመነበት፤

ይህንን አላማ ከግብ ለማድረስ የታክስ ማስከፈያ መጣኔው ከወቅታዊው የኢኮኖሚ ሁኔታ ጋር የተጣጣመ እንዲሆን የሚያስችል ማስተካከያ ለማድረግ፤ የታክስ መሰረቱን ለማስፋት እና ውጤታማ የሆነ የታክስ ማበረታቻ ስርዓት አጠቃቀም እንዲኖር ለማድረግ፤

ለታክስ ማጭበርበር ምቹ ሁኔታን ከፈጠሩ አፈጻጸሞች አንዱ በጥሬ ገንዘብ የሚፈጸም ክፍያ በመሆኑ፤ በዚህ እና በሌሎች መንገዶች ከታክስ ለመሸሽ የሚደረገውን ጥረት ለመከለካል በሚያስችል መንገድ የተወሰኑ የገቢ ግብር አዋጅ ድንጋጌዎችን በማሻሻል የታክስ ስርአቱ መሠረታዊ የታክስ መርሆዎችን ለማሳካት በሚያስችል መልኩ እንዲቀረጽ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ - መንግስት አንቀጽ 55(1) እና (11) በተደነገገው መሰረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የገቢ ግብር (ማሻሻያ) አዋጅ ቁጥር / 2017" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. ማሻሻያ

የፌዴራል የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 979/2008 እንደሚከተለው ተሻሽሏል፦

1. ከአዋጁ አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 27 ቀጥሎ የሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀጽ 28፣ 29 እና 30 ተጨምረዋል፦

የገንዘብ ሚኒስቴር
የሪከርድ አስተዳደር አገልግሎት 2

"(28) "በጠቅላላ ሽያጭ ላይ የሚከፈል ግብር" ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 49 የተመለከቱት አነስተኛ ግብር ከፋዮች ከንግድ ስራቸው ባገኙት አመታዊ ጠቅላላ ሽያጭ ላይ ተሰልቶ ግብር የሚከፈልበት ቀለል ያለ የግብር ስርአት ነው።

(29) "ከዲጂታል ይዘት ፈጠራ የሚገኝ ገቢ" ማለት አንድ ግለሰብ ወይም ድርጅት የቪዲዮ ማጋሪያ አገልግሎቶችን፣ የማህበራዊ ሚዲያ መድረኮችን፣ የድምጽ ማስተላለፊያ (ፖድካስት) አገልግሎቶችን እና የቀጥታ ስርጭት መድረኮችን ጨምሮ በኦንላይን መድረኮች ላይ ዲጂታል ይዘትን በመፍጠር እና በማሰራጨት የሚያገኘው ማንኛውም የገንዘብ ወይም በአይነት የሚገኝ ገቢ ነው። ይህም የሚከተሉትን ገቢዎች ያካትታል፦

ሀ/ ማስታወቂያዎች እና ስፖንሰርሺፖች፣

ለ/ የምርት ስም ስምምነቶች እና ድጋፎች፣

ሐ/ የአጋርነት ግብይት እና የምርት ምደባዎች፣

መ/ የደጋፊዎች አስተዋጽኦ፣ የገንዘብ ስጦታዎች ወይም የብዙሃን የገንዘብ ማሰባሰብ (ክራውድ ፈንዲንግ)፣

ሠ/ የአባልነት ክፍያዎች፤

ረ/ የዲጂታል ወይም የአካላዊ ሸቀጦች ሽያጭ፣

ሰ/ ለማስተዋወቂያ እንቅስቃሴ ምትክ የተገኙ ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች፣ እና

ሸ/ ከዚህ በላይ ከተጠቀሱት ጋር ተመሳሳይነት ያላቸው ሌሎች ክፍያዎች።

(30) "የዲጂታል አገልግሎት" ማለት የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ የሚወሰን የዲጂታል ይዘት ያለው አገልግሎት ነው።"

2. የአዋጁ አንቀጽ 3 ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ 3 ተተክቷል።

"3. የግብር ከፋይ ደረጃዎች

1/ ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም ሲባል የሚከተሉት የግብር ከፋይ ደረጃዎች ይኖራሉ፤

ሀ) የደረጃ "ሀ" ግብር ከፋይ፤

1) ድርጅት፤ ወይም

2) ጠቅላላ አመታዊ ገቢው ብር 2 ሚሊዮን (ሁለት ሚሊዮን ብር) ወይም ከዚያ በላይ የሆነ ማንኛውም ሌላ ሰው፤

ለ) ደረጃ "ለ" ግብር ከፋይ የሚባለው ድርጅትን ሳይጨምር አመታዊ ጠቅላላ ገቢው ከብር 2 ሚሊዮን (ሁለት ሚሊዮን ብር) የሚያንስ ሰው ነው።

2/ የታክስ ባለሥልጣኑ ታክስ ከፋዩ የሚያቀርበውን የግብር ማስታወቂያ ወይም የሚያገኘውን ሌላ ማናቸውም መረጃ መሠረት በማድረግ ለግብር ዓመቱ የግብር ከፋዩ ደረጃ የተለወጠ መሆን አለመሆኑን ይወስናል።

3/ ሚኒስትሩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከተውን እና ግብር ከፋዮችን የደረጃ "ሀ" ወይም የደረጃ "ለ" ግብር ከፋይ ብሎ ለመመደብ የሚያስችለውን አመታዊ ጠቅላላ ገቢ መጠን በኢኮኖሚ ጥናት ላይ በመመስረት ቢያንስ በአምስት አመት አንድ ጊዜ ማሻሻል አለበት።

3. የአዋጁ አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ 2 (ሐ) እና 3 ተሽረው በሚከተሉት አዲስ አንቀጽ 2(ሐ) እና 3 ተተክተዋል፦

"2(ሐ) ማናቸውም ሰው ተቀጣሪዎችን ወይም ሌሎች ሰራተኞችን በመመደብ የቴክኒክ አገልግሎት እና የምክር አገልግሎትን ጨምሮ የሚሰጠውን አገልግሎት በሚመለከት፤ አገልግሎቱ ወይም ተያያዥ የሆነው በኢትዮጵያ ውስጥ የሚከናወነው የንግድ ስራ በአንድ የግብር አመት ወይም በማናቸውም በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ በጠቅላላው ድምር ከ91 (ዘጠና አንድ) ቀናት በላይ የተከናወነ ከሆነ፤

"3" የግንባታ ስራው የሚከናወንበት ቦታ፤ ፕሮጀክቱ ወይም የስራ እንቅስቃሴው በአንድ የግብር አመት ወይም በማናቸውም አንድ አመት ጊዜ ውስጥ ከ91 (ዘጠና አንድ) ቀናት በላይ የሚቆዩ እስከሆነ ድረስ የህንጻ ግንባታው የሚከናወንበት ቦታ ወይም የኮንስትራክሽኑ ስራ፤ የመገጣጠሚያው ወይም የተከላው ፕሮጀክት ወይም ከነዚህ ጋር የተያያዙ የቁጥጥር ስራዎች በቋሚነት የሚሰራ ድርጅት እንደሆኑ ይቆጠራል።

4. ከአዋጁ አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ 5 ቀጥሎ የሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀጽ 6 እና 7 ተጨምረዋል።

የገንዘብ ሚኒስቴር
የሪከርድ አስተዳደር አገልግሎት 2

"6/ ለዚህ አንቀጽ አፈጻጸም "የቴክኒክ አገልግሎት" ማለት የቴክኒክ፣ የአስተዳደር ወይም የምክር አገልግሎት ባህሪ ያላቸውን አልግሎቶችን የሚያካትት ሲሆን፣ የሚከተሉትን ይጨምራል፦

ሀ) የሂሳብ አያያዝ፣

ለ) የኦዲት፣

ሐ) የኢኮኖሚና ኢንቨስትመንት፣

መ) የፋይናንስ፣

ሠ/ የህግ፣

ረ) የአስተዳደር፣

ሰ) የኢንጂነሪንግ፣

ሸ) የአርኪቴክቸር፣

ቀ) የቅየሳ፣

በ) የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጅ፣

ተ) ማህበራዊ ጉዳይ፣ ወይም

በሌላ ተመሳሳይ መስክ የሚሰጥ የሙያ አገልግሎት::

7. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 6 በተዘረዘሩት የሙያ መስኮች የሚሰማሩ ግብር ከፋዮች የግብይታቸው መጠን ከግምት ውስጥ ሳይገባ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 86 መሰረት የሂሳብ መዝገብ የመያዝ ግዴታ አለባቸው::

5. ከአዋጁ አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 5 ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ 6 ተጨምሯል::

"6. በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነ ሰው በኢትዮጵያ ውስጥ የዲጂታል አገልግሎት በመስጠት የሚያገኘው ገቢ በኢትዮጵያ የተገኘ ገቢ እንደሆነ ይቆጠራል"

6. ከአዋጁ አንቀድ 8 ንዑስ (2) ቀጥሎ የሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀጽ (3)፣ (4)፣ (5) እና (6 ) ተጨምረዋል::

"3/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ቢኖርም፣ አንድ ግለሰብ ከአንድ በላይ፣

ሀ) ቀጣሪ፣ ወይም

የገንዘብ ሚኒስቴር የሪከርድ አስተዳደር አገልግሎት 2

ለ) በአንቀጽ 49 ስር ከሚወድቅ የንግድ ስራ ገቢ በስተቀር በሰንጠረዥ ሀ፤ ለ ወይም ሐ መሰረት ግብር የሚከፈልበት ገቢ ያለው ከሆነ፤

አግባብ ያለው የፌዴራል ታክስ ባለስልጣን ከተለያዩ የገቢ ምንጮች የተገኘውን ታክስ የሚከፈልበት ገቢ በአንድነት በማጠቃለል ግብሩን ማስላት አለበት።

4/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 መሰረት ግብሩ ከተሰላ በኋላ ግብር ከፋዩ በከፈሉ ገቢ ላይ ለሌላ በህግ ስልጣን ለተሰጠው አካል ግብር የከፈለ መሆኑ ከተረጋገጠ የከፈለው ታክስ ሊከፍል ከሚገባው ታክስ ጋር እንዲካካስ ይደረጋል።

5/ ማናቸውም ተቀጣሪ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 በተመለከተው መሰረት ከተለያየ ምንጭ ገቢ የሚያገኝ ከሆነ በመቀጠር ካገኘው ገቢው ላይ ተቀንሶ የተከፈለው ግብር የመጨረሻ አይሆንም። ስለሆነም በአዋጁ አንቀጽ 83(2) መሰረት የተጠቃለለውን ገቢውን የማስታወቅ ግዴታ አለበት።

6/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 6 መሰረት የተጠቃለለው ገቢ በፌዴራል መንግስት ደረጃ ታክስ የሚሰላበት ታክስ ከፋዩ የፌዴራል እና የክልል ታክስ ከፋይ በሚሆንበት ጊዜ ሲሆን፤ ታክሱ በአዋጁ አንቀጽ 11(2) መሰረት አግባብነት ያለውን መጣኔ ተፈጻሚ በማድረግ ከተሰላ በኋላ አግባብ ላለው ክልል የተከፈለው ታክስ ተቀናሽ የሚደረግ ይሆናል።"

7. **የአዋጁ አንቀጽ 11 ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ 11 ተተክቷል፦**

**"11. በመቀጠር በሚገኝ ገቢ ላይ ተፈጻሚ የሚሆኑ መጣኔዎች**

በመቀጠር በሚገኝ ወርሃዊ ገቢ ላይ ለሚጣለው ግብር ተፈጻሚ የሚሆኑት መጣኔዎች የሚከተሉት ናቸው፦

| በየወሩ ከመቀጠር የሚገኝ ገቢ (ብር) | በመቀጠር በሚገኝ ገቢ ላይ ተፈጻሚ የሚሆን መጣኔ |
|---|---|
| 0 -2,000 | 0% |
| 2,001-4,000 | 15% |
| 4,001-7,000 | 20% |
| 7,001-10,000 | 25% |
| 10,001 -14,000 | 30% |
| ከ14,000 በላይ | 35% |

የገንዘብ ሚኒስቴር የሪከርድ እስተዳደር አገልግሎት 2

8. ከአዋጁ አንቀድ 12 ንዑስ አንቀጽ (4) ቀጥሎ የሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀጽ (5)፣ (6) እና (7) ተጨምረዋል::

"5/ የዚህ አዋጅ አንቀጽ 93 እንደተጠበቀ ሆኖ፤ የታክሱ ባለስልጣን ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ጋር በመተባበር ለግብር አሰባበሰብ አላማ በአንቀጽ 93(1) የተጠቀሱት ተቋማት ውስጥ የሚሠሩ ሠራተኞች ዝርዝር እና አድራሻ ለማግኘት የሚያስችል ሥርዓት ያቋቁማል::

6/ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኙ የውጭ አገር ኤምባሲዎች እና ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ውስጥ ተቀጥረው የሚሠሩ ሠራተኞችን የሚመለከት መረጃ የመሰብሰብ እና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 5 መሠረት በሚቋቋመው ሥርዓት በሚወሰነው መንገድ እና የጊዜ ገደብ ውስጥ ይህንን መረጃ ለታክሱ ባለሥልጣን የማስተላለፍ ኃላፊነት አለበት::

7/ በኢትዮጵያ ውስጥ ለውጭ ሠራተኞች ማንኛውንም ዓይነት የሥራ ፈቃድ የመስጠት ወይም የማደስ ኃላፊነት የተሰጣቸው ሁሉም የመንግሥት አካላት ፈቃድ የተሰጠ ወይም እድሳት የተደረገ ስለመሆኑ ወዲያውኑ ለታክሱ ባለሥልጣን ማሳወቅ አለባቸው:: በዚህ መልኩ የሚሰጠው ማስታወቂያ የሠራተኛውን ሙሉ ስም፣ በኢትዮጵያ የሚገኘውን አድራሻውን፣ የአሠሪውን ስም፣ የሥራ ፈቃዱን ዓይነት፣የቆይታ ጊዜ፣ ደመወዝ እና ሌሎች የአይነት ጥቅማ ጥቅሞች እንዲሁም በታክሱ ባለሥልጣን ሊጠየቅ የሚችል ማንኛውንም ሌላ ተገቢ መረጃን ማካተት አለበት፤

9. የአዋጁ አንቀጽ 14 ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) ተሰርዘው በሚከተሉት አዲስ አንቀጽ (1) እና (2) ተተክተዋል፦

"14. የኪራይ ገቢ ግብር

1/ በድርጅቶች ኪራይ ገቢ ላይ ተፈጻሚ የሚሆነው የግብር መጣኔ 30% (ሰላሳ በመቶ) ነው::

2/ በግለሰቦች የኪራይ ገቢ ላይ ተፈጻሚ የሚሆኑት መጣኔዎች የሚከተሉት ናቸው፦

የገንዘብ የሪከርድ አስተዳደር አገልግሎት 2 ሚኒስቴር

| አመታዊ ግብር የሚከፈልበት የኪራይ ገቢ (በብር) | የኪራይ ገቢ ግብር መጣኔ |
|---|---|
| 0-24,000 | 0% |
| 24,001-48,000 | 15% |
| 48,001-84,000 | 20% |
| 84,001-1120,000 | 25% |
| 1120,001-168,000 | 30% |
| Over 168,000 | 35% |

10. "ከአዋጁ አንቀፅ 15 ንዑስ አንቀፅ 7 ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀፅ 8 ተጨምሯል፡

"8 ለዚህ አንቀፅ አፈፃፀም "ከቤት ኪራይ የሚገኝ ገቢ" ማለት ለማናቸውም አገልግሎት ከሚውል ህንፃ፣ ከመኖሪያ ቤት፣ ለመጋዘን አገልግሎት ከሚውል ህንፃ ኪራይ የሚገኝ ገቢ ሲሆን የኢንዱስትሪ ፓርክ አልሚ የሚገነባቸውን የኢንዱስትሪ መሰረተልማቶች እና በካፒታል ዕቃ ኪራይ ንግድ ሥራ መሠረት የንግድ ስራ ሀብት ሆነው የሚከራዩ ህንፃዎችን ወይም ግሪን ሃውስ እና በመጋዘን ውስጥ ዕቃ የሚያከማቹ ሰዎች የሚከፍሉትን ክፍያ አይጨምርም።"

11. የአዋጁ አንቀጽ 19 ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) ተሰርዘው በሚከተሉት አዲስ አንቀጽ (1) እና (2) ተተክተዋል። እንዲሁም አዲስ ንዑስ አንቀጽ 3 እና 4 ተጨምሯል።

"19. በንግድ ሥራ ገቢ ላይ ተፈጻሚ የሚሆኑ መጣኔዎች

1/ በድርጅት ላይ ተፈፃሚ የሚሆነው የንግድ ሥራ ገቢ ግብር መጣኔ 30% (ሠላሳ በመቶ) ነው።

2/ በግለሰብ ላይ ተፈጻሚ የሚሆኑት የንግድ ስራ ገቢ ግብር መጣኔዎች የሚከተሉት ናቸው።

የገንዘብ ሚኒስቴር የሪከርድ አስተዳደር አገልግሎት 2

| ከንግድ ስራ የሚገኝ ግብር የሚከፈልበት ገቢ በአመት | የንግድ ስራ ገቢ ግብር መጣኔ |
|---|---|
| 0-24,000 | 0% |
| 24,001-48,000 | 15% |
| 48,001-84,000 | 20% |
| 84,001-120,000 | 25% |
| 1120,001-168,000 | 30% |
| ከ168,000 በላይ | 35% |

አንቀጽ የተደነገገው ቢኖርም ኃላፊነቱ የተወሰነ የሽርክና ማህበር እና በህጋዊ መንገድ የተመዘገበ የጋራ የኢንቨስትመንት ፈንድ በማናቸውም የሕግ ቅርጽ ቢቋቋምም በድርጅት ደረጃ የሚያገኘው ገቢ ግብር አይከፈልበትም። ሆኖም ኃላፊነቱ የተወሰነ የሽርክና ማህበር ለአባላቱ በሚያከፋፍለው ገቢ ላይ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 2 ስር ባለው ሰንጠረዥ "ሐ" መሰረት ግብሩን ቀንሶ ለታክሱ ባለስልጣን ገቢ ማድረግ አለበት። የጋራ የኢንቨስትመንት ፈንድ ለባለአክሲዮኖች ከሚያከፋፈለው ትርፍ ላይ በአዋጁ አንቀጽ 57 መሰረት የትርፍ ድርሻ ግብር ቀንሶ ገቢ ማድረግ አለበት። የዚህ ንዑስ አንቀጽ ዝርዝር አፈፃፀም የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ ይወሰናል።

4/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የኢንቨስትመንት ፈንድ ድርጅቱ እና ኃላፊነቱ የተወሰነ የሽርክና ማህበሩ በዚህ አዋጅ የተደነገጉት ሌሎች ግዴታዎች ተፈፃሚ ይሆኑበታል።

12. ከአዋጁ አንቀጽ 21 ቀጥሎ የሚከተሉት አዲስ አንቀጽ 22 እና 23 ተጨምረዋል፡አዲስ አንቀጽ 22 እና 23 በመግባቱ ምክንያት በነባሩ አዋጅ ከአንቀጽ 22 ጀምሮ ያሉት ድንጋጌዎች በቅደም ተከተል ከአንቀጽ 24 በመጀመር ተሸጋሽገዋል።

"22. ከዲጂታል ይዘት ፈጠራ የሚገኝ ገቢ

1/ ከዲጂታል ይዘት ፈጠራ የሚገኝ ገቢ የሚከተሉትን ሁኔታዎች ካሟላ የንግድ ገቢ ተደርጎ ይወሰዳል፦

ሀ/ ትርፍ ለማግኘት ታስቦ በመደበኛነት የሚከናወን ከሆነ፤
ለ/ ፈጣሪው በሙያዊ ወይም በተደራጀ መንገድ የሚንቀሳቀስ ከሆነ፤ እና
ሐ/ የንግድ መዝገቦች የሚያዙ ከሆነ ወይም ከንግድ ጋር የተያያዙ ወጪዎች የሚደረጉ ከሆነ።

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከቱት ሁኔታዎች ካልተሟሉ፣ ገቢው እንደ ሌላ ገቢ ተመድቦ በዚህ አዋጅ ሠንጠረዥ "መ" መሠረት ግብር የሚጣልበት ሲሆን ዝርዝር አፈፃፀሙ የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ ይወሰናል።
3/ የታክሱ ባለሥልጣን የዲጂታል ይዘት ፈጠራ የንግድ እንቅስቃሴ መሆኑን ለመወሰን መመሪያዎች ያወጣል፤ በተለይም የገቢውን መጠን፣ የግብይቶችን ብዛት፣ የይዘቱን ዓይነት እና የንግድ ዓላማውን ከግምት ውስጥ ያስገባል።
4/ በኢትዮጵያ ለሚኖሩ ዲጂታል ይዘት ፈጣሪዎች ክፍያዎችን የሚያመቻች ማንኛውም የኦንላይን መድረክ፣ ዓመታዊ ገቢያቸው የገንዘብ ሚኒስቴር በሚያወጣው መመሪያ ከሚወስነው ገደብ በላይ ከሆነ ለእያንዳንዱ ፈጣሪ ያገኙትን ጠቅላላ ገቢ በየዓመቱ ለታክሱ ባለስልጣን ሪፖርት ማድረግ አለበት።
5/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 መሰረት በኦንላይን መድረክ ሪፖርት የተደረገም ይሁን ያልተደረገ ከዲጂታል ይዘት ፈጠራ የሚገኝ ማንኛውም ገቢን በተመለከተ፣ ገቢው በደረሰው ሰው በዓመታዊ የገቢ ግብር ማስታወቂያው ላይ መገለጽ አለበት።
6/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ከተወሰነው ገደብ በላይ ገቢ የሚያገኝ ዲጂታል ይዘት ፈጣሪ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ማግኘት እና ሁሉንም ተፈጻሚነት ያላቸውን የግብር ግዴታዎችን መወጣት አለበት።

"23. አማራጭ አነስተኛ ግብር

1/ በዚህ አዋጅ በሌሎች አንቀጾች ወይም በሌላ ማናቸውም ህግ የተደነገገው ቢኖርም፤ ማናቸውም ድርጅት ወይም ሰው ግብር በሚወሰንበት የግብር አመት ከሁሉም የንግድ ስራ የገቢ ምንጮች ባገኘው ትርፍ ላይ ሊከፍል የሚገባው ግብር በዚሁ የግብር አመት ካገኘው ጠቅላላ ገቢ ከ2.5% (ከሁለት ነጥብ አምስት በመቶ) በታች ከሆነ ግብር ከፋዩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 በተመለከተው የማስከፈያ መጣኔ መሰረት አማራጭ አነስተኛ ግብር መክፈል አለበት።

የሪከርድ አስተዳደር አገልግሎት 2 ሚኒስቴር

2/ በዚህ አንቀጽ መሰረት አማራጭ አነስተኛ ግብር የሚከፈለው በሚከተለው የማስከፈያ መጣኔ ይሆናል፦

ሀ) የድርጅቱ አመታዊ ጠቅላላ ገቢ 2.5%፤ ወይም

ለ) ባንኮችን በሚመለከት ከባንክ ስራ የተገኘ የተጣራ ገቢ 2.5%፤

ሐ) የኢንሹራንስ ኩባንያዎችን በሚመለክት ከህይወት እና ከህይወት ውጪ ከሆነ ኢንሹራንስ የተገኘው ጠቅላላ አረቦን 2.5%፤

መ) ዋጋቸው የተወሰነ ዕቃዎችን አቅራቢ ድርጅትን በሚመለከት የኮሚሽን ገቢው 2.5%፤

3/ በዚህ አንቀጽ መሰረት የሚከፈለው አማራጭ አነስተኛ ግብር በአዋጁ አንቀጽ 18 መሰረት ከሚከፈለው የንግድ ትርፍ ግብር ላይ ተቀናሽ ይደረጋል፡፡

4/ የዚህ አንቀጽ ድንጋጌ በአዋጁ አንቀጽ 49 መሰረት በጠቅላላ ገቢው ላይ ግብር በሚከፍል ግብር ከፋይ ላይ ተፈጻሚ አይሆንም፡፡

5/ በዚህ አንቀጽ መሰረት ግብር ከፋዩ የከፈለው ግብር ሊከፍል ከሚገባው የንግድ ትርፍ ላይ የሚቀነሰው በሚከተለው አኳኋን ይሆናል፦

ሀ) እስከ 5 (አምስት) አመታት ድረስ፤

ለ) በአዋጁ አንቀጽ 18 መሰረት ሊከፈል ከሚገባው የንግድ ትርፍ ግብር ላይ የሚቀነሰው ሂሳብ በዚህ አንቀጽ መሰረት ሊከፈል እስከሚገባው አማራጭ አነስተኛ ግብር ድረስ ሆኖ፤ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት የተከፈለውን ተቀናሽ የተደረገበት የንግድ ትርፍ ግብር ሳይጨምር ይሆናል፡፡

6/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 እንደተጠበቀ ሆኖ፤ የሚከተሉት ከአማራጭ አነስተኛ ግብር ነጻ ተደርገዋል፦

ሀ) በኪሳራ ምክንያት መፍረስ ላይ ያለ ድርጅት፤ እና

ለ) በእዳ ማሸጋሸግ ላይ ያለ ድርጅት፡፡

7/ የዚህ አንቀጽ ድንጋጌ በኢንቨስትመንት ማበረታቻ ህግ መሰረት የግብር እፎይታ በተሰጠው ሰው ላይም ተፈጻሚ ይሆናል፡፡ ስለሆነም አማራጭ አነስተኛ ግብሩ የተሰጠው ማበረታቻ ተቀንሶ ሊከፈል በሚገባው የገቢ ግብር ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

8/ ለዚህ አንቀጽ አፈጻጸም፦

ሀ) "አመታዊ ጠቅላላ ገቢ" ማለት በግብር አመቱ ከተከናወነ የዕቃ ሽያጭ እና አገልግሎት ያመስጠት ተግባር የተገኘ ጠቅላላ ገቢ ነው፡፡

የሪከርድ አስተዳደር አገልግሎት 2 ሚኒስቴር

ለ) "ከባንክ ስራ የተገኘ ገቢ" ማለት ከሚከተሉት ምንጮች የተገኘ ገቢ ነው፡-

(i) ብድርን ከመሳሰሉት የባንኩ ሃብቶች በሚገኝ ወለድ እና ተቀማጭ ሂሳብን ለመሳሰሉት የባንኩ እዳዎች በሚከፈል ወለድ መካከል ያለው ልዩነት፤

(ii) ግብይትን፤ ሂሳብ ማስተዳደርን እና የምክር አገልግሎትን ከመሳሰሉ አገልግሎቶች የሚገኝን ገቢ ጨምሮ ከክፍያዎች እና ከኮሚሽኖች የሚገኝ ገቢ፤

(iii) በፋይናንስ ሰነዶች በመገበያየት የሚገኝ ትርፍ እና የሚያጋጥም ኪሳራን ጨምሮ ከግብይት የሚገኝ የተጣራ ገቢ፤

(iv) ለግብይት ወም ለኢንቨስትመንት አላማ ከተያዙ የፋይናንስ ሰነዶች የሚገኝ ጠቅላላ ገቢ፤ እና

(v) አስቀድሞ ከሂሳብ መዝገብ የተሰረዙ ሂሳቦችን ከማስመለስ እና ከመሳሰሉት የተለያዩ ገቢዎች የተገኘ የሌሎች የስራ እንቅስቃሴዎች ገቢ።

ሐ) "የኮሚሽን ገቢ" ማለት በህግ ወይም በተዋዋዮች መካከል በተደረገ ውል በተወሰነው መሰረት ከአንድ ዕዕቃ ወም አገልግሎት ዋጋ ላይ ለአገልግሎት ሰጪው የሚከፈል ገንዘብ ነው።

(መ) "ዋጋው የተወሰነ ድርጅት" ማለት ዕቃዎችን የሚሸጥበት ወይም አገልግሎትን የሚያቀርብበት ዋጋ በውል ወይም በመንግስት አካል የተወሰነ ወይም ቁጥጥር የሚደረግበት ድርጅት ነው።

13. የአዋጁ አንቀጽ 24 (1) (ለ) እና (2) ወይም በተሻጋሸገው አንቀጽ 26 (1) (ለ) እና (2) ተሰርዘው በሚከተሉት አዲስ አንቀጽ 24 (1) (ለ) እና (2) ተተክተዋል፡-

"1/ (ለ) የፌዴራል መንግስት የሚኒስትሮች ምክር ቤት ወይም የክልል መንግስት ካቢኔ ባደረገው ጥሪ መሰረት የአገሪቱን አንድነት እና ሉዓላዊነትን ለማስከበር ወይም ሰው ሰራሽ ወይም የተፈጥሮ አደጋ ወይም ወረርሽኝ ለመከላከል ለተመሳሳይ ጥሪዎች ምላሽ ለመስጠት ወይም የገንዘብ ሚኒስቴር በሚያወጣው መመሪያ ለተዘረዘሩ ማህበራዊ ስራዎች የሚውል ከሆነ ነው።

የገንዘብ ሚኒስቴር
የሪከርድ አስተዳደር አገልግሎት
2

2/ በዚህ አንቀጽ መሰረት ለግብር ከፋዩ የሚፈቀደው ጠቅላላ ተቀናሽ ከግብር ከፋዩ ግብር የሚከፈልበት የግብር አመቱ ገቢ 10% ( አስር በመቶ) መብለጥ የለበትም። ሆኖም የገንዘብ ሚኒስቴር በሚያወጣው መመሪያ ለተወሰኑ መንግስት ቅድሚያ ለሚሰጣቸው ዘርፎች የሚደረገው ድጋፍ ከዚህ መጠን ከፍ እንዲል ሊፈቅድ ይችላል።

14. ከአዋጁ አንቀጽ 27 ንዑስ አንቀጽ 1 ተራ ፊደል (ነ) በተሻሻለው አንቀጽ 29 ንዑስ አንቀጽ 1 ተራ ፊደል (ነ) ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ ተራ ፊደል (ኘ) ተጨምሯል፡

"ኘ. ማናቸውም ግብር ከፋይ ወደ ባንክ ሂሳብ ገቢ ከሚደረግ ቼክ፤ ወደ ባንክ ሂሳብ ገቢ ከሚደረግ የባንክ ድራፍት፤ ከአንድ የባንክ ሂሳብ ወደሌላ የባንክ ሂሳብ እና ወይም በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ፈቃድ በተሰጣቸው የክፍያ መፈጸሚያ መንገዶች ገንዘብ ከማስተላለፍ ውጪ በአንድ ቀን ውስጥ ለአንድ ሰው ከብር 30,000 (ሰላሳ ሺህ ብር) በላይ በሆነ ጥሬ ገንዘብ የፈጸመው ወይም የፈጸማቸው ክፍያዎች፤

15. የአዋጁ አንቀጽ 33 ተሰርዟል።

16. የአዋጁ አንቀጽ 49 ወይም በተሻሻለው አንቀጽ 50 ተሽሮ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ 50 ተተክቷል፦
"50. የደረጃ "ለ" ግብር ከፋዮች ግብር አከፋፈል

1/ በዚህ አዋጅ በሌሎች አንቀጾች ወይም በሌላ የታክስ ህግ የተደነገገው ቢኖርም የደረጃ "ለ" ግብር ከፋዮች ግብር የሚከፍሉት በጠቅላላ ገቢያቸው ላይ ይሆናል።
2/ ግብሩ የሚጣለው እና የሚከፈለው በግብር አመቱ ውስጥ ከዕቃ እና ከአገልግሎት ሽያጭ በሰበሰቡት ጠቅላላ የሽያጭ ገቢ ላይ ነው።
3/ በዚህ አንቀጽ መሰረት የሚከፈለው ግብር ማስከፈያ መጣኔ የሚከተለው ይሆናል፦

| *ግብር የሚከፈልበት አመታዊ ጠቅላላ ገቢ* | *መጣኔ (በመቶኛ)* |
|---|---|
| *0 — 100,000* | 2% |
| *100,001 — 500,000* | 3% |
| *500,001 — 1,000,000* | 5% |
| *1,000,001 — 1,500,000* | 7% |
| *1,500,001 — 2,000,000* | 9% |

ገንዘብ
የሪከርድ
አስተዳደር
አገልግሎት
2
ሚኒስቴር

4/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ ለሚከተሉት ተፈጻሚ አይሆንም፦

ሀ) የሚከተሉትን ጨምሮ የሙያ አገልግሎት ለሚሰጡ ሰዎች፦

(1) ለሂሳብ አያያዝ ሙያ፤

(2) ለአርኪቴክቶች፤

(3) ለአማካሪዎች፤

(4) ለግንባታ ስራ ተቋራጮች፤

(5) ለመሃንዲሶች፤

(6) ለፋይናንስ፣ ለኢኮኖሚ እና ኢንቨስትመንት ባለሙያዎች፤

(7) ለጤና ባለሙያዎች፤

(8) ለህግ ባለሙያዎች፤

ለ) ለተጨማሪ እሴት ታክስ ለተመዘገቡ ታክስ ከፋዮች፤ እና

ሐ) የሂሳብ መዝገብ በማቅረብ በሠንጠረዥ "ሐ" መሰረት በተጣራ ታክስ የሚከፈልበት ገቢ ላይ ግብር ለመክፈል ለመረጡ የደረጃ "ለ" ግብር ከፋዮች፤

5/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 4 በተዘረዘሩት ሙያዎች የተሰማሩ ግብር ከፋዮች በዚህ አዋጅ ለደረጃ "ሀ" የሚጠየቀውን የሂሳብ መዝገብ የመያዝ ግዴታ አለባቸው።

6/ የደረጃ "ለ" ግብር ከፋዮች በእያንዳንዱ የግብር ዓመት የንግድ ሥራ ገቢ ግብር የሚከፍሉት የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ በሚወሰነው የግብር አከፋፈል ዘዴ ነው።

17. የአዋጁ አንቀጽ 51 ንዑስ አንቀጽ (2) ወይም በተሻሻለው አንቀጽ 52 ንዑስ አንቀጽ (2) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ 52 (2) ተተክቷል፦

"52 (2) በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነ ሰው ግብር የሚከፍልበት መጣኔ፦

ሀ) ለመድን በሚከፈል አረቦን ወይም የሮያልቲ በጠቅላላ ክፍያ ላይ 15% (አስራ አምስት በመቶ)፤

ለ) በትርፍ ድርሻ በጠቅላላ ገቢ ላይ 15% (አስራ አምስት በመቶ)፤

ሐ) በወለድ ጠቅላላ ገቢ ላይ 10% (አስር በመቶ)፤

መ) ከስራ አመራር ክፍያ ወይም ከቴክኒክ አገልግሎት ክፍያ ላይ ከጠቅላላ ገቢው 15% (አስራ አምስት በመቶ)፤

18. ከአዋጁ አንቀጽ 51 ወይም በተሸጋሸገው አንቀጽ 52 ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ አንቀጽ 53 ተጨምሯል፦

"53. የዲጂታል አገልግሎት ግብር

1. በኢትዮጵያ ውስጥ የዲጂታል አገልግሎትን በማቅረብ ገቢ የሚያገኝ ነዋሪ ወይም ነዋሪ ያልሆነ ማንኛውም ሰው የሚያገኘው ገቢ ግብር ይከፈልበታል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት የሚከፈለው ግብር ከ 5% ( አምስት በመቶ) የማይበልጥ ሲሆን የማስከፈያው መጣኔ፣ የአከፋፈሉ ሁኔታ እና ሌሎች ዝርዝር ጉዳዮች የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ ይወሰናል፡፡"

19. የአዋጁ አንቀጽ 53 ንዑስ አንቀጽ 1 ወይም በተሸጋሸገው አንቀጽ 55 ንዑስ አንቀጽ 1 ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ 1 ተተክቷል፦

"1/ በኢትዮጵያ በሚካሄድ የመዝናኛ አገልግሎት ተሳታፊ የሆነ በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነ የመዝናኛ አገልግሎት የሚሰጥ ሰው ወይም ቡድን ከመዝናኛ አገልግሎት በሚያገኘው ገቢ ላይ 15% (አስራ አምስት በመቶ) ግብር ይከፍላል፡፡"

20. የአዋጁ አንቀጽ 54 ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 ወይም በተሸጋሸገው አንቀጽ 56 ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 ተሰርዞ በሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 ተተክቷል፦

"1/ በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነ ሰው የሮያልቲ ገቢ ያገኘ እንደሆነ፤-

ሀ) በጠቅላላ የሮያልቲ ክፍያ ላይ 15% (አስራ አምስት በመቶ)፤ ወይም

ለ) የሮያልቲ ገቢው የተገኘው ከኪነጥበብ ወይም ከባህላዊ ስራ ከሆነ 10% (አስር በመቶ)፤

የገቢ ግብር የመክፈል ግዴታ አለበት፡፡

2/ በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነ ሰው በቋሚነት በሚሰራ ድርጅት አማካኝነት በኢትዮጵያ ውስጥ የሮያልቲ ገቢ ያገኘ እንደሆነ በጠቅላላ የሮያልቲ ገቢው ላይ 15% (አስራ አምስት በመቶ) የገቢ ግብር የመክፈል ግዴታ አለበት፡፡"

የገንዘብ ሚኒስቴር የሪከርድ አስተዳደር አገልግሎት 2

21. የአዋጁ አንቀጽ 55 ወይም በተሸጋሸገው አንቀጽ 57 ድንጋጌ ተሽሮ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ 57 ተተክቷል፤

"57. የትርፍ ድርሻ

1/ በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነና የትርፍ ድርሻ ያገኘ ሰው በጠቅላላው የትርፍ ድርሻ ገቢ ላይ 15% (አስራ አምስት በመቶ) የትርፍ ድርሻ የገቢ ግብር የመክፈል ግዴታ አለበት::

2/ በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነ ሰው ኢትዮጵያ ውስጥ ባለው በቋሚነት በሚሠራ ድርጅት አማካይነት በኢትዮጵያ ውስጥ የትርፍ ድርሻ ገቢ ሲያገኝ በጠቅላላ የትርፍ ገቢው ላይ 15% (አስራ አምስት በመቶ) የገቢ ግብር የመክፈል ግዴታ አለበት::

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው ቢኖርም አንድ ድርጅት በኢትዮጵያ ውስጥ ላቋቋመው በቋሚነት የሚሰራ ድርጅት ወይም የኩባንያዎች ቡድን አባል ለሆነ በኢትዮጵያ ውስጥ ነዋሪ ለሆነ ድርጅት የአክሲዮን ድርሻ ያከፋፈለ እንደሆነ የዚህ አዋጅ አንቀጽ 53 ድንጋጌዎች በድርጅቱ ላይ ተፈጻሚ አይሆኑም::

4/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 መሰረት ከተከፋፈለው ሃብት ጋር በተያያዘ የሚፈቀድ ወይም ተቀናሽ የሚደረግ ወጪ የሌለ ሲሆን፤ ግብር ከፋዩ የተከፋፈለውን ገንዘብ ማስተካት ወይም ማካካስ ወይም ገንዘቡ በተላለፈበት አመት ይህንን ሂሳብ በግብር አመቱ የግብር ከፋዩ ገቢ ውስጥ ማካተት የለበትም::

5/ ለዚህ አንቀጽ አፈጻጸም "የኩባንያዎች ቡድን" ማለት አንድ ኩባንያ (ከዚህ በኋላ "ተቆጣጣሪው የቡድኑ ኩባንያ" እየተባለ የሚጠራው በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ ከአንድ በላይ በሆኑ ኩባንያዎች (ከዚህ በኋላ "በቁጥጥሩ ስር ያሉ ኩባንያዎች" ተብለው በሚጠሩት) ውስጥ 50% (ሃምሳ በመቶ) እና ከዚያ በላይ ያሉ አክሲዮኖች ያሉት እንደሆነ ነው::

22. የአዋጁ አንቀጽ 56 ወይም በተሸጋሸገው አንቀጽ 58 ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ ተተክቷል፡

"58. ወለድ

1/ በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነ ሰው የወለድ ገቢ ያገኘ እንደሆነ በጠቅላላው የወለድ ገቢ ላይ 10% (አስር በመቶ) ግብር ይከፍላል::

2/ በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነ ሰው ኢትዮጵያ ውስጥ ባለው በቋሚነት በሚሰራ ድርጅት አማካኝነት በኢትዮጵያ ውስጥ የወለድ ገቢ ያገኘ እንደሆነ በጠቅላላው የወለድ ገቢ ላይ 10% (አስር በመቶ) ግብር ይከፍላል፡፡

3/ በዚህ አንቀጽ የተደነገገው ቢኖርም አንድ የፋይናንስ ተቋም በሌላ የፋይናንስ ተቋም ገንዘብ በማስቀመጥ ወይም በሌላ ተያያዥ አገልግሎት የሚያገኘው ወለድ በሰንጠረዥ "ሐ" መሰረት ግብር የሚከፈልበት ይሆናል፡፡

4/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው ቢኖርም ማናቸውም ግብር ከፋይ ዕቃን ወይም አገልግሎትን በዱቤ በመሸጥ የሚያገኘው ወለድ በሰንጠረዥ "ሐ" መሰረት ግብር የሚከፈልበት ይሆናል፡፡"

23. **የአዋጁ አንቀጽ** 57 **ንዑስ አንቀጽ** (1) **ወይም በተሸጋሸገው አንቀጽ** 59 **ንዑስ አንቀጽ** (1) **ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ** (1) **ተተክቷል፦**

"(1) በኢትዮጵያ ውስጥ በሚደረጉ የዕድል ሙከራ ጨዋታዎች ተሳትፎ ገቢ ያገኘ ሰው ባገኘው ጠቅላላ ገቢ ላይ 20% (ሃያ በመቶ) የገቢ ግብር የመክፈል ግዴታ አለበት፡፡"

24. **የአዋጁ አንቀጽ** 59 **ንዑስ አንቀጽ** (2)፣(3) **እና** (7) **በተሸጋሸገው አንቀጽ** 61 **ንዑስ አንቀጽ** (2)፣ (3) **እና** (7) **ተሰርዘው በሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀጽ** (2) **እና** (7) **ተተክተዋል፦**

"(2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት በሚከፈለው ግብር ላይ ተፈጻሚ የሚሆነው መጣኔ 15% (አስራ አምስት በመቶ) ይሆናል፡፡

(3) ግብር የሚከፈልበትን ሃብት በማስተላለፍ የሚገኝ ጥቅም ነው የሚባለው በሚከተለው ቀመር ተሰልቶ የሚገኘው ጥቅም ነው፦

(ሀ - ለ)- ሐ = ግብር የሚከፈልበት ጥቅም

ለዚህ ቀመር አፈጻጸም፦
ሀ - ሀብቱ የተላለፈበት ዋጋ
ለ- ሃብቱ የተፈራበት ዋጋ
ሐ- 30% (ሠላሳ በመቶ)

ገንዘብ የሪከርድ አስተዳደር አገልግሎት 2 ሚኒስቴር

(7) ለዚህ አንቀጽ አፈጻጸም፦ "ግብር የሚከፈልበት ሃብት" ማለት አክሲዮን፣ ቦንድ እና ቤት ሲሆን፤ ቤትን በሚመለከት ቤቱ ከመተላለፉ በፊት ለሁለት አመታት ሙሉ በሙሉ ለመኖሪያነት ያገለገለ ህንጻን አይጨምርም።"

25. ከአዋጁ አንቀጽ 59 ወይም ከተሸጋሸገው አንቀጽ 61 ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ አንቀጽ 62 ተካቷል፦

"62. ከኢትዮጵያ ውጭ የሚፈጸም ቀጥተኛ ያልሆነ ዝውውር

1/ የማናቸውም ሰው ወይም ድርጅት ታክስ የሚከፈልበት ገቢ፤ ገቢው ከተገኘበት ቀን በፊት ባለው የ365 ቀናት ጊዜ ውስጥ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ አንድ ወይም ከአንድ በላይ በሆኑ የተሳሰሩ ኩባንያዎች አማካኝነት በኢትዮጵያ ውስጥ ከሚገኝ የማይንቀሳቀስ ንብረት ወይም ሌላ ማናቸውም ንብረት ጋር የተያያዘውን አክሲዮን ወይም የአባልነት መብት ዋጋ ከ20% በላይ በመሸጥ የተገኘውን ገቢ ይጨምራል።

2/ ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 አፈጻጸም ታክስ በሚከፈልበት ገቢ ውስጥ የሚጠቃለል ጥቅም ነው የሚባለው፦

(ሀ) ጥቅሙ ከመገኘቱ በፊት በነበረው የ365 ቀን ጊዜ ውስጥ ከተሸጠው አክሲዮን ወይም ሌላ ጥቅም ዋጋ ውስጥ ከ50 በመቶ በላይ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ ኢትዮጵያ ውስጥ ካለ የማይንቀሳቀስ ወይም ሌላ ማናቸውም ንብረት ጋር የተገኘው ጥቅም ሙሉ በሙሉ፤ ወይም

(ለ) በሌላ ማናቸውም ሁኔታ በሚከተለው ቀመር መሰረት ተሰልቶ የሚገኘው ጥቅም፦

ሀxለ/ሐ

ለዚህ ቀመር አፈጻጸም፦

ሀ - የተገኘው ጥቅም የገንዘብ መጠን፤

ለ - በኢትዮጵያ ውስጥ ከሚገኘው የማይንቀሳቀስ ንብረት ወይም ሌላ ማናቸውም ንብረት ጋር የተያያዘ አክሲዮን ወይም ሌላ ጥቅም ዋጋ፤ እና

ሐ - የጥቅሙ ጠቅላላ ዋጋ፤

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 መሰረት ግብር የሚከፈልበት ገቢ ያለው በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነ ወይም ነዋሪ ያልሆነ ሰው ያገኘው ወይም ያስተላለፈው ንብረት በኢትዮጵያ ውስጥ እንደሆነ እና ጥቅሙም

የተገኘው ምንጩ ከኢትዮጵያ ገቢ እንደሆነ ተቆጥሮ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 61 መሰረት ግብር ይከፈልበታል።

4/ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኘው እና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 የተጠቀሰውን የማይንቀሳቀሰው ወይም ሌላ ማናቸውም ንብረት ላይ ቀጥተኛ ባለቤትነት ያለው ሰው በተዘዋዋሪ መንገድ አንድ ወይም ከአንድ በላይ በሆኑ የተሳሰሩ ኩባንያዎች አማካኝነት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከተው ግብይት የተከናወነ እንደሆነ ይህንኑ ግብይት ወዲያውኑ ለባለሥልጣኑ በፅሁፍ ማሳወቅ አለበት።

5/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት የሚያስተላልፈው ሰው የኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነ እንደሆነ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኘው እና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 የተጠቀሰውን ንብረት የሚያስተላልፈው ሰው በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነው ሰው ወኪል እንደሆነ ተቆጥሮ ከማስተላለፉ ጋር ተያይዞ በዚህ አዋጅ መሠረት ሊከፈል የሚገባውን ግብር የመክፈል ግዴታ አለበት።

6/ በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነ ድርጅት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 መሰረት ግብር የሚከፈልበትን በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነ ሰው ወይም ድርጅት ያስተላለፈ ወይም የማስተላለፉን ተግባር ያመቻቸ እንደሆነ ግብሩ በሌላ ሰው ካልተከፈለ እንደወኪል ተቆጥሮ በአዋጁ አንቀጽ 61 የተመለከተውን ታክስ እንዲከፍል ይገደዳል።

7/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከተውን ንብረት ያስተላለፈ ሰው ወይም ድርጅት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 83 መሰረት ለታክሱ ባለስልጣን ያስተለተላለፈው ንብረት የገቢ ማስታወቂያ ማቅረብ አለበት።

8/ በዚህ አንቀጽ መሰረት ለታክሱ ባለስልጣን ያስለተላለፈው ንብረት ማስታወቂያ የማቅረብ ግዴታውን ያልተወጣ ሰው ወይም ድርጅት በታክስ አስተዳደር አዋጅ በተደነገገው መሰረት ቅጣት ይጣልበታል።

26. የአዋጁ አንቀጽ 61 ወይም የተሻሻለው አንቀጽ 64 ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ 64 ተተክቷል፦

"64. ያልተከፋፈለ ትርፍ

1/ ሚኒስትሩ በሚያወጣው መመሪያ መሰረት በአንድ የግብር አመት ግብር ከተከፈለ በኂላ ለአባለቱ ያልተከፋፈለ እና መልሶ ኢንቨስት ያልተደረገ የተጣራ የድርጅቱ ትርፍ 15% (አስራ አምስት በመቶ) ግብር ይከፈልበታል።

2/ ለዚህ አንቀጽ ዓላማ "ያልተከፋፈለ ትርፍ" ማለት የኩባንያው የሒሳብ ዓመት ካለቀ በኂላ ባሉት አስራ ሁለት (12) ወራት ውስጥ

የሪከርድ አስተዳደር አገልግሎት 2 ሚኒስቴር

ለባለአክሲዮኖች ያልተከፋፈለ ወይም የኩባንያውን ካፒታል ለመጨመር ያልዋለ ወይም የኩባንያውን አክሲዮን ለመግዛት ያመለከቱ ባለአክሲዮኖችን የአክሲዮን ዋጋ ለመክፈል ያልዋለ የተጣራ ትርፍ ሲሆን፤ ኢትዮጵያ ውስጥ ባለው በቋሚነት በሚሰራ ድርጅት አማካኝነት የንግድ ስራ ለሚያካሂድ የውጭ አገር ኩባንያ ያልተላከ ትርፍን ያካትታል፡፡

3/ ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ የሚወሰኑ ዝርዝር ሁኔታዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ አንድ ኩባንያ ትርፉን መልሶ ኢንቨስት እንዳደረገ የሚታሰበው፣ የተጣራ ትርፉን የባለአክሲዮኖቹን አክሲዮን እና የኩባንያውን ካፒታል ለማሳደግ ሲጠቀምበት ወይም የተጣራ ትርፉን ባለአክሲዮኖች ለመግዛት ቃል ከገቡት አክሲዮን ውስጥ ያልተከፈለውን ቀሪ ሂሳብ ለመክፈል ሲጠቀምበት ነው፡፡

27. የአዋጁ አንቀጽ 62 ወይም በተሻሻለው አንቀጽ 65 ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ 65 ተተክቷል፡-

"65. በቋሚነት በሚሰራ ድርጅት የሚላክ ትርፍ

"(1) በኢትዮጵያ ውስጥ በቋሚነት በሚሰራ ድርጅት አማካኝነት የንግድ ስራ የሚያከናውን በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነ ሰው በኢትዮጵያ ውስጥ ካለው በቋሚነት ከሚሰራ ድርጅት የሚላክለት ትርፍ ላይ 15% (አስራ አምስት በመቶ) ግብር የመክፈል ግዴታ አለበት፡፡

(2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከተው በቋሚነት የሚሰራ ድርጅት ትርፉን የግብር አመቱ ከተጠናቀቀበት ቀን ጀምሮ በ12 (አስራ ሁለት) ወራት ውስጥ ያልላከ ቢሆንም እንደላከ ተቆጥሮ ግብሩን እንዲከፍል ይደረጋል፡፡ ሆኖም ይህ ትርፍ ወደ ውጭ በሚላክበት ጊዜ በድጋሚ የሚከፈል ግብር አይኖርም፡፡

(3) የዚህ አንቀጽ አፈጻጸም የሚመራው የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ መሰረት ይሆናል፡፡

28. ከአዋጁ አንቀጽ 65 ንዑስ አንቀጽ (1) (ከ) ወይም በተሻሻለው አንቀጽ 68 ንዑስ አንቀጽ 1 (ከ) ቀጥሎ የሚከተሉት ተራ ፊደል (ነ)፤(ኘ )፤ (አ) ተጨምረዋል፡-

"(1) (ነ) የኢትዮጵያ የተቀማጭ ገንዘብ መድን ፈንድ የሚሰበስበው አረቦን፤

(ኘ) በስራ ላይ ያሉ ኩባንያዎች ከአዲስ ከሚያወጡት አክሲዮን የሚገኝ የካፒታል ዋጋ እድገት ጥቅም (ፕሪሚየም)፤

የገቢዎች አስተዳደር አገልግሎት 2 ሚኒስቴር

(ለ) ማናቸውም ኩባንያ በኩባንያው ውስጥ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ ከአስራ ሁለት ነጥብ አምስት በመቶ (12.5%) ያላነሰ ድምጽ የመስጠት መብት እና የኩባንያውን ውሳኔዎች የመቆጣጠር መብት ላለው በኢትዮጵያ ነዋሪ ለሆነ ኩባንያ የሚፈጽመው የአክሲዮን ትርፍ ድርሻ ክፍያ፤"

29. **ከአዋጁ** አንቀጽ 77 ወይም በተሻሻለው አንቀጽ 80 ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ አንቀጽ 81 ተጨምሯል፤

"82. ክፍያ የሚፈጸምባቸው ዘዴዎች

1/ ማናቸውም ግብር ከፋይ ወደ ባንክ ሂሳብ ገቢ በሚደረግ ቼክ፤ ወደ ባንክ ሂሳብ ገቢ በሚደረግ የባንክ ድራፍት፤ ከባንክ ሂሳብ ወደ ባንክ ሂሳብ ገንዘብ በማስተላለፍ ወይም በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ፈቃድ በተሰጣቸው የክፍያ መፈጸሚያ መንገዶች ካልሆነ በስተቀር ከዚህ በታች ለተዘረዘሩት ግብይቶች ከብር 30,000 (ሰላሳ ሺህ ብር) በላይ የሆነ ጥሬ ገንዘብ መቀበል አይችልም።

ሀ) በአንድ ቀን ውስጥ ከአንድ ሰው ጋር በተደረገ ጠቅላላ ግብይት፤ ወይም

ለ) ከአንድ ግብይት ጋር በተያያዘ የሚፈጸም ክፍያ፤ ወይም

ሐ) ከአንድ ሰው ጋር ከተፈጸመ አንድ ግብይት ወይም ተግባር ጋር የተያያዘ ክፍያ፤

2/ **በዚህ** አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው በሚከተሉት ላይ ተፈጻሚ አይሆንም፤

ሀ) በመንግስት መስሪያ ቤቶች፤ በመንግስት የልማት ድርጅቶች፤ በባንኮች እና በማይክሮ ፋይናንስ ድርጅቶች፤

ለ) የገንዘብ ሚኒስቴር በሚያወጣው መመሪያ የሚዘረዘሩ ሰዎች ወይም ድርጅቶች ወይም የተለዩ ግብይቶች፤

3/ ለዚህ አንቀጽ አፈጻጸም "ግብይት" ማለት ግብር የመክፈል ግዴታ የተጣለበት ሰው የሚያከናውነው በዚህ አዋጅ መሰረት ግብር የሚከፈልበት የስራ እንቅስቃሴ ነው።

የገንዘብ
የሪከርድ አስተዳደር አገልግሎት
2
ሚኒስቴር

4/ የገንዘብ ሚኒስቴር በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከተውን የገንዘብ መጠን ሊያሻሽል ይችላል፡፡"

30. የአዋጁ አንቀጽ 82 ንዑስ አንቀጽ 2 ወይም በተሻጋሸገው አንቀጽ 86 ንዑስ አንቀጽ 2 ተሰርዟል።

31. የአዋጁ አንቀጽ 82 ንዑስ አንቀጽ 3 ወይም በተሻጋሸገው አንቀጽ 86 ንዑስ አንቀጽ 3 ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ 3 ተተክቷል፦

"3/ የደረጃ "ለ" ግብር ከፋዮች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 86(1) መሰረት የሂሳብ መዝገብ መያዝ ይችላሉ፡፡ የያዙት የሂሳብ መዝገብ ተቀባይነት ካገኘ የሚከፍሉት ግብር የሚወሰነው በሂሳብ መዝገባቸው መሰረት ይሆናል"

32. የአዋጁ አንቀጽ 82 ንዑስ አንቀጽ 6 ወይም በተሻጋሸገው አንቀጽ 86 ንዑስ አንቀጽ 6 ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ 6 ተተክቷል፤ እንዲሁም አዲስ ንዑስ አንቀጽ 7 እና 8 ተጨምሯል፤

"6/ በታክስ አስተዳደር አዋጁ የተቀመጡት ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ ግብር ከፋዩ አንድ ወጪ በተቀናሽነት እንዲያዝለት ወይም በአንድ ሀብት ዋጋ ውስጥ እንዲካተትለት የሚያስችለውን የሰነድ ማስረጃ ማቅረብ ያልቻለ እንደሆነ ባለሥልጣኑ ወጪ በተቀናሽነት እንዲያዝ ወይም አንድ ወጪ በአንድ ሀብት ዋጋ ውስጥ እንዲካተት ላይፈቅድ ይችላል፡፡

7/ ማናቸውም ግብር ከፋይ በዚህ አዋጅ መሰረት ሊይዝ የሚገባውን የሒሳብ መዝገብ ካላቀረበ ግብሩ በግምት ይወሰናል፡፡ ሆኖም ለደረጃ "ለ" በተቀመጠው የማስከፈያ ዘዴ መሰረት ሊስተናገድ አይችልም፡፡

8/ ማናቸውም ግብር ከፋይ በሌላ ኩባንያ ውስጥ አክሲዮን ለመግዛት በተበደረው ገንዘብ ላይ የሚከፍለው ወለድ በወጪነት ይያዛል፡፡"

33. በአዋጁ ከአንቀጽ 82 ንዑስ አንቀጽ 7 ወይም በተሻጋሸገው አንቀጽ 86 ንዑስ አንቀጽ 7 ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ አንቀጽ 86 (8) ተጨምሯል፤ የነባሩ አዋጅ ንዑስ አንቀጽ (7) ንዑስ አንቀጽ 9 በሚል ተተክቷል፦

"8) በሠንጠረዥ 'ሐ' መሠረት ግብር የመክፈል ግዴታ ያለበት እና ከአንድ በላይ የንግድ ሥራ መስክ ገቢ የሚያገኝ የደረጃ "ሀ" ግብር ከፋይ፣ በዚህ አዋጅ እና በሌሎች ተፈጻሚነት ባላቸው ሕጎች መሠረት ለእያንዳንዱ የተለየ የሥራ መስክ የሂሳብ መዝገቦችን እና ደጋፊ መረጃዎችን በተናጠል መያዝ አለበት፡፡"

የሪከርድ
አስተዳደር
አገልግሎት
2
ሚኒስቴር

34. የአዋጁ አንቀጽ 83 ንዑስ አንቀጽ(2) እና (3) ወይም በተሻሻለው አንቀጽ 87 ንዑስ አንቀጽ(2) እና (3) ተሰርዘው በሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀጽ (2) እና (3) ተተክተዋል፦

"(2) አንድ ተቀጣሪ በአንድ አመት ውስጥ ከአንድ በላይ የሆነ ቀጣሪ ያለው ከሆነ ወይም በዚህ አዋጅ አንቀጽ 10 በተመለከተው መሰረት በዚሁ አመት ውስጥ በሌላ ሰንጠረዥ ስር የሚወድቅ ገቢ ያለው ከሆነ ወይም ከራሱ ገቢ ላይ ግብር ቀንሶ የመክፈል ግዴታ ያለበት ከሆነ፤ አመቱ በተጠናቀቀ በ30 ቀን ጊዜ ውስጥ የተጠቃለለውን ገቢውን ማስታወቅ አለበት።

(3) የተጠቃለለውን ገቢውን የማስታወቅ ግዴታ ለሌለበት ተቀጣሪ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 96 መሰረት ቀጣሪው በየአመቱ የሚሰጠው ከተከፋዩ ሂሳብ ላይ ግብር መቀነሱን የሚያረጋግጠው ማስረጃ ለዚህ አዋጅ እና ለታክስ አስተዳደር አዋጅ አፈጻጸም ተቀጣሪው ለአመቱ ሊከፍል ለሚገባው ግብር በማስረጃነት የሚያገለግል ይሆናል።"

35. ከአዋጁ አንቀጽ 83 ወይም በተሻሻለው አንቀጽ 87 ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ አንቀጽ 88 ተጨምሯል፤

"88. አስተዳደራዊ መቀጫ

በዚህ አዋጅ አንቀጽ 78 የተደነገገውን በመተላለፍ በአንቀጹ ከተመለከተው መጠን በላይ በጥሬ ገንዘብ ክፍያ የተቀበለ ግብር ከፋይ በብልጫ የተቀበለውን ገንዘብ እጥፍ አስተዳደራዊ ቅጣት ይቀጣል።"

36. የአዋጁ አንቀጽ 84 ንዑስ አንቀጽ 2 እና 4 ወይም በተሻሻለው አንቀጽ 89 ንዑስ አንቀጽ 2 እና 4 በሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀጽ 2 እና 4 ተሸረው ተተክተዋል፤ እንዲሁም አዲስ ንዑስ አንቀጽ 5 ተካቷል፤

"2/ የደረጃ "ሀ" ግብር ከፋዮች ዓመታዊ ግብር የሚከፍሉት በሚከተለው አኳኋን ይሆናል፤

ሀ) ከተያዘው የግብር ዓመት በፊት በነበረው የግብር ዓመት የከፈሉትን ግብር 25% (ሃያ አምስት በመቶ) የሂሳብ ሪፖርት

ከሚያቀርቡበት ወር መጨረሻ ጀምሮ በሚቆጠር በየሦስት ወሩ በ5 (አምስት) የሥራ ቀናት ውስጥ አስቀድመው ይከፍላሉ፤

ለ) የሂሳብ ሪፖርት በሚያቀርቡበት ወር መጨረሻ በሂሳብ ሪፖርቱ መሰረት ሊከፍሉ ከሚገባው ግብር ላይ በየሦስት ወሩ የከፈሉት ተቀንሶ ቀሪውን ይከፍላል፤

4/ የደረጃ "ለ" ግብር ከፋዮች ዓመታዊ ግብር የሚከፍሉት በሚከተለው አኳኋን ይሆናል፤

ሀ) ከተያዘው የግብር ዓመት በፊት በነበረው የግብር ዓመት የከፈሉትን ግብር 25% (ሃያ አምስት በመቶ) ከሐምሌ ወር መጨረሻ ጀምሮ በሚቆጠር በየሦስት ወሩ በ15 (አስራ አምስት) የሥራ ቀናት አስቀድመው ይከፍላሉ፤

ለ) በየግብር ዓመቱ ሐምሌ ወር መጨረሻ ሊከፍሉ ከሚገባው ግብር ላይ በየሦስት ወሩ የከፈሉት ተቀንሶ ቀሪውን ይከፍላሉ፤"

5/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 እና 4 የተደነገገው ቢኖርም ለመጀመሪያ ጊዜ የገቢ ግብር የሚከፍሉ አዲስ ግብር ከፋዮች የመጀመሪያውን የግብር ዓመት በተመለከተ ዓመታዊ ግብር የሚከፍሉት በሚከተለው አኳኋን ይሆናል፤

ሀ) የደረጃ "ሀ" አዲስ ግብር ከፋዩች ዓመታዊ ገቢያቸውን ማስታወቅ ባለባቸው ጊዜ በግብር ዓመቱ ሊከፍሉት የሚገባውን ግብር መክፈል አለባቸው።

ለ) የደረጃ "ለ" አዲስ ግብር ከፋዮች ከሐምሌ 1 ቀን እስከ ሐምሌ 30 ቀን ባለው ጊዜ ውስጥ ግብሩን መክፈል አለባቸው።

37. የአዋጁ አንቀጽ 92 ንዑስ አንቀጽ 1 ወይም በተሻሻለው አንቀጽ 97 ንዑስ አንቀጽ 1 ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (1) ተተክቷል

"1/ ከጥቃቅን ኢንተርፕራይዝ በስተቀር ማንኛውም ድርጅት፤ የመንግስት መስሪያ ቤት፤ ለትርፍ ያልተቋቋመ ድርጅት ወይንም መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት ባላስልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ ግብር ቀንሰው እንዲያስቀሩ ኃላፊነት የተሰጣቸው ግብር ከፋዮች ለሚከተሉት ግብይቶች ከሚፈጽሙት ጠቅላላ ክፍያ ላይ 3% (ሶስት በመቶ) ግብር ቀንሰው የማስቀረት ግዴታ አለባቸው፦

የገንዘብ
የሪከርድ አስተዳደር አገልግሎት 2
ሚኒስቴር

ሀ) በኢትዮጵያ ውስጥ በአንድ ግገር ወይም በአንድ የዕቃ አቅርቦት ውል ከብር 20,000 (ሃያ ሺህ ብር) በላይ ለሆነ የዕቃ አቅርቦት የሚፈጸም ክፍያ፤

ለ) በኢትዮጵያ ውስጥ በአንድ የአገልግሎት አቅርቦት ውል ከብር 10,000 (አስር ሺህ ብር) በላይ የሚፈጸም ክፍያ፤"

38. **የአዋጁ አንቀጽ 92 ንዑስ አንቀጽ 4 ወይም በተሻሻለው አንቀጽ 97 ንዑስ አንቀጽ 4 ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (4) ተተክቷል፤**

"4/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ተፈጻሚ የሚሆንበት አቅራቢ ግብር ቀንሶ ለሚያስቀረው ሰው የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥሩን እና የታደሰ ንግድ ፈቃዱን ያልሰጠ እንደሆነ ግብሩን ቀንሶ የማስቀረት ግዴታ ያለበት ሰው ከሚፈጽመው ጠቅላላ ክፍያ ላይ 30% (ሰላሳ በመቶ) ቀንሶ የማስቀረት ግዴታ አለበት::"

39. **ከአዋጁ አንቀጽ 99 ወይም በተሻሻለው አንቀጽ 104 ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ አንቀጽ 105 ተጨምሯል፤**

"105. **የገቢ ግብር ማበረታቻ እና በሌሎች ሕጎች የተሰጡ የገቢ ግብር ነፃ መብቶች አፈፃፀም**

1) በኢንቨስትመንት ሕጉ መሰረት ኢንቨስትመንት ፈቃድ የተሰጣቸው ኢንቨስተሮች ሊሰጣቸው የሚገባው የገቢ ግብር ማበረታቻ የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ በሚወሰነው መሰረት መሆን አለበት::

2) በኢንቨስትመንት ማበረታቻ ደንብ ከተሰጡ ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን መብቶች ውጭ በሌሎች አዋጆች፣ ደንቦች፣ እና መመሪያዎች መሰረት የተሰጡ ማናቸውም ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን መብቶች በዚህ አዋጅ ተሽረዋል::

3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የተደነገገው ቢኖርም፣ በኀብረት ሥራ ማኅበራት አዋጅ በተደነገገው መሰረት ማኅበሩ በሚያገኘው የንግድ ሥራ ገቢ ላይ የገቢ ግብር ተፈፃሚ አይሆንበትም::"

